# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርኀ ግብር

## በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለማዳበር ያለው ፋይዳ ፍተሻ

በ

አሸናፊ ደበበ

የካቲት፣ 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለማዳበር ያለው ፋይዳ ፍተሻ

በ

አሸናፊ ደበበ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርኀ ግብር

ለአማርኛን ማስተማር (TeAm) መርኃግብር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት

አማካሪ

ሙሉሰው አስራት (ዶ/ር)

የካቲት፣ 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

**የድኅረ ምረቃ መርኀ ግብር**

# በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለማዳበር ያለው ፋይዳ ፍተሻ

በ

አሸናፊ ደበበ

2017 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| የአማካሪ ሥም | ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|
| ሙሉሰው አስራቴ (ዶ/ር) | __________ | __________ |
| **የፈታኞች ሥም** | **ቀን** | **ፊርማ** |
| __________ | __________ | __________ |
| __________ | __________ | __________ |

# ምስጋና

በመጀመሪያ የጅማሬና የፍጻሜ ባለቤት የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ከጅማሬዬ እስከፍጻሜዬ ስላልተለየኝ ክብርና ምስጋና ይግባው፡፡

በመቀጠል ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ካላቸው ውድ ጊዜ በመቀነስ የተሳሳትኩትን በማቃናት፣ የማነባቸውን የተለያዩ መጻሕፍትና ምርምሮች በመጠቆም፣ ከመስመር ስወጣ ወደመስመር እንድመለስ በመግራት ትልቅ ሚና የተጫወቱት አማካሪዬና መምህሬ ዶክተር ሙሉሰው አስራቴ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

መረጃ በምሰበስበበት ወቅት አብሮኝ በመገኘት አስፈላጊውን እርዳታ ያደረገልኝ፣ የስታትስቲክስ ስሌቱን በSPSS በመታገዝ በመስራት ላገዘኝ ውድ ጓደኛዬ መምህር አሻግሬ ግባቱ፣ ለፍትነቱ ምቹ የሆነ ዐውድ እንዲኖር ለተጉ በትምህርት ቤቱ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የአስተዳደር አካላት እንዲሁም አስፈላጊውን መረጃ በመስጠትና ለፍትነቱ ፍቃደኛ በመሆን ለጥናቱ ቁልፉን ሚና የተጫወቱ በ2016 ዓ.ም በቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲማሩ የነበሩ የ10B እና 10E ተማሪዎች ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

በአይዞህ ባይነቷ ወደር የሌላት፣ ጥናቱን በሚመለከት አስፈላጊ እገዛ ሲያስፈልገኝ የማስቸግራት፣ እሷም ሳትሰለች የምታግዘኝ ውድ እህቴ ማህደር በቀለ ምስጋና ሲያንስሽ ነው፡፡

በመጨረሻም ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ አስፈላጊ ሀሳቦችን በመስጠትና በማበረታታት፣ የህይወት ስንክሳር በዝቶ ጥናቱን ለማቋረጥ ስገደድ ችግሮቼን ችግርሽ አድርገሽ ጥናቴ ላይ እንዳተኩር ያደረገሽው ውዷ ባለቤቴ መቅደስ ቦጋለ ወሰን አልባ ምስጋናሽን እንቺ!

# የይዘት ማውጫ


ምስጋና................................................................................................................................ i
አጠቃሎ ............................................................................................................................... v
ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ...................................................................................................... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................................................ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት....................................................................................................... 6
1.3 የጥናቱ ዓላማ ...................................................................................................................... 7
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ .................................................................................................................. 8
1.5 የጥናቱ ወሰን....................................................................................................................... 8
1.6 የጥናቱ ውስንነት…………………………..………………………………….....8
1.7 የጥናቱ ቁልፍ ሀረጋት……………………………………………………………….9
ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት ............................................................................................ 10
2.1 የቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች .................................................................................. 10
2.1.1 መምህር ተኮር ዘዴ ........................................................................................................ 10
2.1.2 ዘመናዊ (አሳታፊ) የማስተማሪያ ዘዴ ................................................................................ 11
2.2 ይዘት ተኮር አቀራረብ......................................................................................................... 11
2.2.1 የይዘት ተኮር አቀራረብ ምንነት ........................................................................................ 12
2.2.2 የይዘት ተኮር የማስተማሪያ ስነዘዴ አተገባበር ደረጃዎች ........................................................ 13
2.2.2.1 ቅድመ ትግበራ........................................................................................................... 14
2.2.2.2 ጊዜ ትግበራ ............................................................................................................... 14
2.2.2.3 ድህረ ትግበራ ............................................................................................................. 17
2.2.3 የይዘት ተኮር የማስተማረያ ዘዴ ጠቀሜታዎች ...................................................................... 18
2.3 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት...................................................................................................... 19
ምዕራፍ ሶስት፡- የአጠናን ዘዴ................................................................................................. 22
3.1 የጥናቱ ንድፍ .................................................................................................................... 22
3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ......................................................................................................... 23
3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ................................................................................................ 23
3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ .................................................................................................. 23

3.2.3 የተማሪዎች አመራረጥ ............ 23
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ............ 24
3.4 የጥናቱ ሂደት ............ 25
3.5 የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ............ 25
3.6 የመረጃ ትንተና ዘዴ ............ 26
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተናና የትንታኔው ማብራሪያ ............ 28
4.1 የመረጃ ትንተና ............ 28
4.2 የውጤት ማብራሪያ ............ 30
ምዕራፍ አምስት ............ 33
5.1 ማጠቃለያ ............ 33
5.2 መደምደሚያ ............ 34
5.3 አስተያየት ............ 35
ዋቢ ጽሑፎች ............ 36
አባሪዎች ............ 41
አባሪ 1፡- ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና ............ 41
አባሪ 2፡- የሰዋስው ፈተናውን አስተማማኝነት ለመፈተሽ የተሰበሰበ መረጃ ............ 45
አባሪ 3፡- የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤት ............ 46
አባሪ 4፡- የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤት ............ 48
አባሪ 5፡- የቁጥጥር ቡድኑ የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤት ............ 50
አባሪ 6፡- የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤት ............ 52
አባሪ 7፡- የፈተናው አስተማማኝነት ፍተሻ ስሌት በCronbach's Alpha ............ 54
አባሪ 8፡- የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ በሻፒሮ-ዊልክ ............ 56
አባሪ 9፡- የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ በሻፒሮ-ዊልክ ............ 56
አባሪ 10፡- የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ በተደጋጋሚ አምድ ግራፍ ............ 57
አባሪ 11፡- የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ በተደጋጋሚ አምድ ግራፍ ............ 58

አባሪ 12፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤቶች የፍንግጥ ውጤቶች መኖር አለመኖር ፍተሻ በባለሳጥን ግራፍ.......................................................................................................59
አባሪ 13፡- የድህረትምህርት ፈተና ውጤቶች የፍንግጥ ውጤቶች መኖር አለመኖር ፍተሻ በባለሳጥን ግራፍ.......................................................................................................60
አባሪ 14፡- የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ሰዋስውን በዐውድ ተኮር ለማሰልጠን የሚያገለግል ማሰልጠኛ ማኑዋል..................................................................................................61

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዐውድ በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለመሳካት ጥናቱ ፍትነት መሰል ቅድመና ድሕረትምህርት ባለቁጥጥር ቡድን ንድፍን ተከትሏል፡፡ ለዚህም የቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና የክፍል ደረጃው (አስረኛ ክፍልን) በአመቺ የንሞና ዘዴ፣ ሁለት መማሪያ ክፍሎችን (10B እና 10E) በቀላል የእጣ ንሞና ስልት እንዲሁም በመማሪያ ክፍሎቹ የሚማሩ 95 ተማሪዎች በጠቅላይ የንሞና ስልት በጥናቱ ተሳታፊነት ተመርጠዋል፡፡ ከ95 ተማሪዎች መረጃ የተሰበሰበው በቅድመና ድሕረትምህርት የሰዋስው እውቀት መለኪያ ፈተና ነው፡፡ የፈተናውን አስተማማኝነት ለመፈተሽም በዋናው ጥናት ባልተሳተፉ 25 ተማሪዎች መረጃ ተሰብስቦ የተገኘው መረጃ በCronbach's Alpha ተሰልቶ ውጤቱን ከ0.7 በላይ በመሆኑ ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሏል፡፡ በቅድመትምህርት ፈተናው የተገኘው ውጤት በቁጥጥርና በሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ ስታትስቲካዊ ልዩነት ባለማሳየቱ ፍትነቱ ተካሂዷል፡፡ በድህረትምርት ፈተናው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት የቁጥጥር ቡድን 12.563፣ የሙከራ ቡድን 14.404 ነው፡፡ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ያለው ልዩነት ስታተስቲካዊ ጉልህ መሆኑን ለመፈተሽ በተደረገው የነጻ ናሙና ቲቴስት ፍተሻ በተገኘው ውጤት መሰረት ($t(93) = -3.462$, $P = 0.001$) በቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ይዘት ተኮር የሰዋስው ትምህርት የሰዋስው እውቀትን የመጨመር ፋይዳ እንዳለው መረዳት ተችሏል፡፡ ማስተማሪያ ዘዴው የሰዋስው እውቀትን ከመጨመር አንጻር ያለውን የተጽዕኖ መጠን ለመፈተሽ በተደረገው የCohen's d ፍተሻ ከፍተኛ ተጽዕኖ ($d = 0.71$) እንዳለው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከጥናቱ ውጤት በመነሳት መምህራን የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ለማዳበር ይዘት ተኮር ዘዴን ቢተገብሩ፣ በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወይም ማሻሻል ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች የሰዋስው ትምህርትን አቀራረብና ማስተማሪያ ዘዴ ሲያዘጋጁ ለይዘት ተኮር ዘዴ ትግበራ ምቹ የሆኑ አቀራረቦችንና ማስተማሪያ ዘዴዎችን ቢያካትቱ፣ በሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ምርምር ማድረግ የሚፈልጉ ተመራማሪዎች አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ምርምር ቢያደርጉ የሚሉ የጥናት ጥቆማና አስተያየቶች በአጥኚው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በቋንቋ ትምህርት ከሚሰጡ ይዘቶችና ከሚተኮርባቸው ነጥቦች መካከል አንዱ ሰዋስው ነው፡፡ በማንኛውም የስነ ልሳን ባለሙያ እምነት ከማንኛውም የክህሎት ትምህርት በስተጀርባ ማንኛውም የቋንቋ ተማሪ ሊጨብጠው የሚገባ ጥልቅና ረቂቅ የሆነ የሰዋስው እውቀት አለ (ባየ፣ 2000)፡፡ ይህ የሰዋስው ትምህርት ደግሞ ረጅም እድሜ አለው፡፡ ከዛሬ 2400 አመታት አስቀድሞ ግሪካዊው ፈላስፋ ፕሌቶ ዓረፍተ ነገርን ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ብሎ ከፋፍሎ እንዳሳየና ትምህርቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ እንደመጣ የዘርፉ ምሁራን ይገልፃሉ (Anne, 2007)፡፡ ሰዋስው በቋንቋ ማስተማር ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ የሚመደብ ከመሆኑም ባሻገር ያለሰዋስዋዊ እውቀት ቋንቋን በትክክል መረዳትና ማወቅ እንደሚያስቸግር የምሁራን እምነት ነው (Anne, 2007)፡፡ ይህም የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ለመገልገል በጣም አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

በርካታ ዘመናት ዘልቆ መጀመሪያ በላቲን በኋላም በግሪክ ቋንቋ ይዘወተር የነበረው የመጀመሪያው የቋንቋ  ማስተማሪያ ዘዴ ሰዋስው ወትርጉም የተሰኘው ነበር፡፡ ይህ ስነ ዘዴ እስከ 19ኛው መቶ  ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አጋማሽ ድረስ ስር ሰዶ የቆየ እንደነበረ የስነልሳን ባለሙያዎች ይጠቅሳሉ (Richards & Rodgers, 2001)፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሰዋስው ወትርጉም ዘዴን ተከትለው ሌሎች አዳዲስ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ብቅብቅ ያሉ ሲሆን፣ ቀጥተኛ ዘዴ (Direct method) እና አዳምጦ የመናገር ዘዴ (Audiolingual) ገነው የታዩበት ነበር፡፡ በተለይም ሰዋስው ወትርጉም ዘዴን ስንመለከተው የትምህርቱ ማቅረቢያ ዘዴ ሰዋስው እንደሆነ ስሙ ራሱ ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ታሪክ ትልቅ ቦታ ሲሰጠው የነበረ ነው፡፡

Richards & Rodgers (2001) ቋንቋ ለማስተማር ቀደም ብለው ከተጠቀሱት ዘዴዎች ባሻገር ተግባቦታዊ ዘዴ (Communicative based Instruction)፣ ተራክቧዊ የቋንቋ

ማተማሪያ ዘዴ (Cooprative based Instruction)፣ ይዘት ተኮር ዘዴ (Content based Instruction)፣ እንዲሁም ተግባር ተኮር ዘዴ (Task based Instruction) በተለያየ ጊዜ ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደነበር ገልፀዋል። ከእነዚህም ውስጥ የብዙ አጥኝዎችንና የቋንቋ አስተማሪዎችን ትኩረት እየሳበ የመጣው ይዘት ተኮር ዘዴ እንደሆነ Hardman (2009) እና Snow (1997) ይገልጻሉ። በእርግጥም ዘዴው ቋንቋን ለማስተማር በቀጥታ የቋንቋ ይዘቶችን ከማቅረብ ይልቅ ሌሎች ይዘቶችን በማቅረብ እንዲማሩ የሚያደርግ መሆኑ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ላይ ቁልፍ ቦታ የሚሰጠው ነው። የሰዋስው ትምህርትም እንዲሁ አንደቋንቋ ትምህርት ይዘት በይዘት ተኮር አቀራረብ ቢቀር ተመራጭ መንገድ ነው። በተለይም ከትምህርቱ ይዘት ባህርይ አንጻር የበለጠ ተግባራዊ ቢደረግ ተመራጭ መሆኑን Hardman (2009) ያስረዳሉ። በተጨማሪም ባየ (2000፣xxi) ስለሰዋስው ሲያስረዱ የሚከተለውን ብለዋል።

> በማንኛውም የቋንቋ ሥነልሳን ባለሙያ እምነት ከማንኛውም ክሂሎች ትምህርት በስተጀርባ ማንኛውም የቋንቋ ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባ ጥልቅ እና ረቂቅ የሆነ ዕውቀት አለ። ይኸውም የቋንቋ ሥርዓት ወይም ሰዋስው በመባል የሚታወቅ ክፍል ነው። ይህም ትምህርት የአንድን ቋንቋ ሥርዓት ከድምጽ አሰካኩ እስከ ሐረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው። ይዘቱ የሥርዓት ነው፤ ስለዚህም ከአጠቃቀም ይለያል።

ከባየ ሀሳብ የምንረዳው የቋንቋ ስርዓትና አጠቃቀም ተነጣጥለው የሚታዩ እንደሆኑና የቋንቋውን ሥርዓትና ህግ የሚመለከተው ሰዋስው እንደሆነ ነው። ጌታሁን (1990) ደግሞ ሰዋስው ሁለት አሻሚ ፍችዎች እንዳሉት ያስረዳሉ። የመጀመሪያው በአዕምሮ ውስጥ ያለ የቋንቋ እውቀት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተማሪዎች ስለቋንቋ የሚያደርጉት ገለጻ ነው። የመጀመሪው ፍች ሁሉም ሰው ቋንቋውን መጠቀም የሚያስችለው ችሎታ እንዳለው የሚያስረዳ አዕምሯዊ እሳቤ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው። ሁለተኛው ፍች ደግሞ ከባየ ብያኔ ጋር ይበልጥ የሚቀራረብ ነው። ይህም ያንድን ቋንቋ ሥርዓት የሚመለከት በመሆኑ ከመጀመሪያው ፍች ለየት ይላል።

በሌላ መልኩ Stern (1992)፣ Ur (1988) እና Harmer (1978) ሰዋስው ቃላት ተቀናጅተው ዓረፍተ ነገር የሚመሰርቱበት እና የቋንቋ ስርዓት የሚያጠና ቋንቋ ክፍል መሆኑን ገልጸዋል። ይሄ ሀሳብ ሰዋስው የቋንቋን የአወቃቀር ሥርዓት የሚያጠና መሆኑን ያስረዳል። የተለያዩ የቋንቋ አሀዶች በየደረጃቸው በመቀናጀት እስከትልቁ

መዋቅር (እስከ ዓረፍተ ድረስ) ያለውን የአወቃቀር የሚመለከት ከሆነ ሰዋስው ይባላል ማለት ነው፡፡ ከዓረፍተ ነገር ከፍ እያለ ከሄደ ደግሞ ወደመጻፍ ክሂል ትምህርት ያመራል፡፡

Brown (1994) ሰዋስው የቋንቋ ሥርዓት መሆኑን በመግለጥ ያ ሥርዓት ግን በቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ዘንድ ይሁንታን ያገኘ መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው የአንድ ቋንቋ ሥርዓት ወይም ህግ ህረተሰቡ ልክ ነው ብሎ የተቀበለው መሆን እንደሚኖርበት ነው፡፡ ሀሳቡ የቋንቋ አጠቃቀምንና የቋንቋ ሥርዓትን ሊያቀራርብ የሚችል ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ባየ (2000) እና Brown (1994) የቋንቋ ሥርዓት ተናጋሪዎቹ የሚጠቀሙበት አገባብ ልክ ነው ወይም የተሳሳተ ነው ማለት የሚያስችላቸው እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ሀሳቡን ስናጤነው “ልክ ነው” ወይም “ልክ አይደለም” የሚሉት የቋንቋው ተናጋሪዎች እንደመሆናቸው መጠን ሥርዓቱ ከቋንቋው ተጠቃሚዎች እንደሚቀዳ ያሳየናል፡፡ ይህም ከBrown ሀሳብ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡

የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ Stern (1992) እንደሚያስረዱት የተለያዩ የሀሳብ መለያየቶች አሉ፡፡ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል ቢባልም መካተት የለበትም የሚል ሙግት እንደቀረበበትም አይዘነጋም፡፡ ይህን አስመልክቶ Bygate እና ሌሎች (1994) በአፍ መፍቻ፣ በሁለተኛ ቋንቋም ይሁን በውጭ ቋንቋ ትምህርት በይዘትነት መቅረብ አለበት ወይም የለበትም የሚል ውዝግብ ሲያስነሳ እንደኖረ ጠቅሰዋል፡፡ ይህም የሰዋስው ትምህርት ያስፈልጋልና አያስፈልግም የሚል ሲሆን ለ2000 ዓመታት ሲያከራክር ቆይቷል፡፡ ምሁራኑ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ አመክንዮ በመያዝ በርካታ ሀሳቦችን በማንሳት የተከራከሩ ሲሆን ሀሳባቸውን ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው በሶስት ጎራ ይመደባል፡፡

የመጀመሪያው ጎራ ሰዋሰው በትምህርትነት መሰጠት አለበት የሚሉ ሲሆኑ ከሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች ይልቅ የሰዋስው ትምህርት ቅድሚያ መሰጠት እንዳለበት አበክረው ይከራከራሉ፡፡ ስለሆነም ይህን ሀሳብ በሚያራምዱ ወገኖች አመለካከት የትምህርት ዋናና ተቀዳሚው ግብ የተማሪዎችን የሰዋስው ብቃት ማዳበር ነው፡፡ ሁለተኛው ጎራ ደግሞ ከሰዋስው ትምህርት ይልቅ ለቋንቋ ተግባቦት ልዩ ትኩረት መሰጠት እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ ሀሳባቸውን የሚያራምዱትም ከቋንቋ ትምህርት ዐብይ ዓላማ በመነሳት ነው፡፡ ቋንቋ ለተናጋሪው መግባባት ባለበት መጠን ያግባባ ዘንድ ማስተማር ስላለብን ተማሪዎቹ

የሚማሩትም ተግባቦትን ነው ይላሉ፡፡ ሶስተኞቹ ደግሞ ሁለቱንም ሀሳቦች ሊያስታርቅ የሚችል ሀሳብ አንስተዋል፡፡ ይህም “የቋንቋ ትምህርት ስኬታማ የሚሆነው ሰዋስውንም ሆነ ተግባቦታዊ ክንውኖችን በማቀናጀት ስናስተምር ነው” ሲሉ ያስረዳሉ (Stern, 1992,191)፡፡

በአሁኑ ዘመን የበለጠ እየተሰራበት ያለና ተቀባይነት ያገኘው ሀሳብ ሁለቱን አቀላቅሎ ማስተማር የሚለው ነው፡፡ የቋንቋን ሥርዓት ጠንቅቀው እንዲያውቁ ሰዋስውን ይማራሉ፤ ያወቁትን ሥርዓት በደንብ እንዲጠቀሙበት ደግሞ ለተግባቦት የሚጠቅሙ ትምህርቶችን እናስተምራቸዋለን፡፡ ይህን በተመለከተ ጌታሁን (1990፣v) ሲገልፁ “የቋንቋ ትምህርት ዓላማ በክሂሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በስርዓት ላይም መሆን አለበት” ይላሉ፡፡ ምክኒያቱም ሁለቱም አንድ ቋንቋን ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸውና፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ ተምሬአለሁ የሚለው ሰው እውቀት ቁንፅል ይሆናል ብለዋል፡፡ ይህም ክሂላቱም ሆኑ የሰዋስው ትምህርት ለቋንቋ ትምህርት አስፈላጊዎች እንደሆኑ አመላካች ነው፤ የሰዋስው ትምህርት ከክሂል ትምህር ተለይቶ ሊታይ እንደማይገባው ያሳያል፡፡ ምክኒያቱም አንድ ሰው ሲፅፍ እና ሲናገር የሚያሣየውን ስህተት ወይም ትክክለኛነት በመገምገም ለስህተቱም ሆነ ለትክክለኛነቱ ምክኒያት ለማቅረብ ቋንቋውን ከማወቅ አልፎ የቋንቋውን ስርዓት ማወቅና በውል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የክሂል መለኪያ መስፈርቱ ሰውስው መሆኑን ያመለክታል፡፡

የተገለጸው ውዝግብ ቢኖርም በትምህርትነት ከመቅረብ አልተገደበም፡፡ ከትምህርትነት እንዲገለል ያልተደረገበት ጉዳይም ለአጠቃላዩ የቋንቋ ትምህርት ጉልህ ሚና ስላለው ነው፡፡ ባየም (2000) የአንድን ቋንቋ አጠቃቀሙን ብቻ ካወቀ ተማሪ በተሻለ አጠቃቀሙን ማለትም ክህሎቱን ከነስርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የተሻለ እውቀት እንዳለው ገልጸዋል፡፡ ይህም የክህሎት ትምህርት የተቃና የሚሆነው ከሰዋስው ትምህርት ጋር አብሮ ሲቀርብ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ በፊት በነበረው የሰዋስው ትምህርት ታሪክ በየዘመናቱ የፈለቁት ንድፈ ሀሳቦች ሰዋስውን ከክሂላት ጋር አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያዳግቱ ነበሩ፡፡

የአንድን ትምህርት ይዘት የምናቀርበው ቋንቋ በመጠቀም ነው፡፡ ማንኛውም ይዘት ካለቋንቋ መቅረብ አይችልም፡፡ ቋንቋም ይዘትን ተሸክሞ ወደተፈለገው ቦታ ለማድረስ

ያስችላል፡፡ ይህ ተመጋጋቢነታቸው ደግሞ በትምህርቱ ዓለም ላይም የሚከሰት ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት በእውነተኛው ዐውድ ውስጥ በማስገባት የሚሰጥ ከሆነ ትምህርቱ እንዲሰርጽ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያበረክታል፡፡ ስለዚህ ቋንቋን ለማስተማር ይዘቶችን መጠቀም ለትምህርቱ ስኬታማነት ወሳኝ ነው (Hardman, 2009)፡፡ ይህ መሆን የሚችለው ደግሞ ሰዋስዋዊ ህግጋቱ ሳይፋለስ ሊባል የተፈለገውን ነገር ማንጸባረቅ ሲቻል ነው፡፡

ሰዋስው አንዱ የቋንቋ ትምህርት ክፍል እንደመሆኑ መጠን ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ማስተማር እንችላለን፡፡ በዚህ ዘዴ ሰዋስውን ስናስተምር ትኩረት የምናደርገው ሰዋስው በተለያዩ አሃዶች ውስጥ ያለውን ፋይዳ ማሳየት ላይ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች በራሳቸው ስራ ላይ ወይም በሌሎች አሃዶች ላይ ያለውን ሰዋስዋዊ ሁኔታ እንዲያዩ ያደርጋል፡፡ በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር ከሌሎች የተለመዱ የሰዋስዋዊ ዘዴዎች ልዩ የሚያደርገውም በዓረፍተ ነገር ደረጃም ብቻ ሳይሆን በአንቀጽ ወይም በውህድ አሃድ ላይ ያለውን ሰዋስዋዊ ሁኔታ አግባባዊ በሆነ መልኩ መገንዘብ ማስቻሉ ነው፡፡ በተጨማሪም በሰዋስው ትምህርት ለተማሪዎች ሐሳብና አስተምህሮን እንዲሁም ትርጉም ያለው አውድን ለመፍጠር ያስችላቸዋል፡፡

በሌላ በኩል በይዘት ተኮር ዘዴ የሰዋስው ትምህርት ሲሰጥ ብቻውን አይመጣም፡፡ ጎን ለጎንም የቋንቋውን መድበለ ቃላት ፍቺ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ ይዘት ተኮር ዘዴን በመጠቀም ሰዋስውን ማስተማር የትኩረት ነጥቡ ይዘትና የቋንቋ ቅርፅን አቀናጅቶ ማቅረቡ ላይ ስለሚሆን አካዳሚያዊ (ትምህርታዊ ተግባሩ) ሰዋስውን ከይዘት ጋር በማገናኘት በንፅፅር ማሳየቱ ላይ ይሆናል፡፡

ይሁን (2013) እና ሽፈራው (2013) ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ ተስፋዬ (2012) ሰዋስውን በግልጽ መማር በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም ያለውን ፋይዳ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ ውበቱ (2011) ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እና የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ያለው ውጤታማነት በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣

እንዲሁም ሌሎች አጥኝዎችም ከተጠቀሱት ጥናቶች ጋር ተቀራራቢ ጥናቶችን አጥንተዋል፡፡

ይሁን (2013) እና ሽፈራው (2013) ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በዘጠነኛ ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት በማድረግ ዘዴዎቹ የሰዋስው እውቀትን እንደሚጨምሩ አሳይተዋል፡፡ በተመሳሳይ ተስፋዬ (2012) ሰዋስውን በግልጽ መማር በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም አዎንታዊ ፋይዳ እንዳላቸው፣ ውበቱ (2011) ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እንደሚጨምር አሳይተዋል፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ ሌሎች አጥኚዎች ያላዩት ሰዋስውን በይዘት ተኮር ዘዴ ማስተማር የሰዋስውን እውቀት ከመጨመር አንጻር ያለው ፋይዳ ተፈትሿል፡፡

በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የተማሪዎችን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን ከዚህ ጥናት ጋር ይቀራረባሉ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ስር ሰዋሰውን መሰረት ያደረጉ በርካታ ጥናቶች ቢኖሩም ሰዋስውን በይዘት ተኮር ዘዴ ማስተማር ላይ ግን የተሰራ ጥናት አልታየም፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት ትኩረት በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

Ur (2006) የቋንቋ ተማሪ ቋንቋውን በሚገባ እንዲጠቀም የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊና ወሳኝ እንደሆነ ሲያስረዱ Cunningsworth (1995) ሰዋስውን ያላካተተ መማር ማስተማር ሂደት የተሟላ ነው ለማለት እንደሚያስቸግር ገልጸዋል፡፡ ይህም የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ተዘጋጅቶ መቅረቡ ምን ያህል አስፈላጊ እና ወሳኝ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ርቱዕነት በልማድ ሊገኝ ይችላል፡፡ ትክክለኛነትን ለማግኘት ግን ቋንቋውን ስርዓት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የቋንቋውን ስርዓት ለማወቅ ደግሞ የሰዋስው ትምህርቱን ወይም ስርዓቱን መማር አስፈለጊ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህ ቢሆንም በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የተማሪዎች የሰዋስው እውቀት ማነስ ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ነው (ሙሉጌታ፣ 1996፤ ዮሐንስ፣ 2003፤ አዲስዓለም፣ 2012)፡፡

ሙሉጌታ (1996) የሰዋሰው ትምህርት ክፍል ውስጥስላለው አተገባበር፣ ዮሐንስ (2003) የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሁኔታ አተገባበር ግምገማ እና አዲስዓለም (2012) የኦሮምኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በሚጽፉት ድርሰት ላይ የሚስተዋሉ አሉታዊ የሰዋስው ተጽዕኖዎች እና የግድፈት ምንጮች ፍተሻ ሲያጠኑ የተማሪዎች የሰዋስው እውቀት በጣም ዝቅ ያለ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ አሚናት (2016) ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት በርከት ያለ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን እንደፈጸሙ በጥናታቸው አሳይተዋል፡፡ ከአጥኚው ልምድ አንጻርም በተለያዩ ተከታታይ ጊዜያት ተማሪዎች ሰዋስውን በቀጥታ ከተማሩ በኋላ፣ በምዘና ወቅት ዝቅተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ስነ ዘዴ በተለይ ይዘት ተኮርን በመጠቀም ኢቀጥተኛ በሆነ መልኩ ሰዋስውን ማስተማር ሊኖረው የሚችለውን ፋይዳ ለመፈተሽ ጥናቱን ለማከናወን ተነስቷል፡፡

በመሆኑም ጥናቱ ሁለት መሪ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተጠንቷል፤ ጥያቄዎቹም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

1. በይዘት ተኮር ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?
2. ይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን በመጨመሩ ረገድ ፋይዳ ካለው የተጽዕኖው መጠን ምን ያህል ነው?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዐውድ በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ መፈተሽ ነው፡፡ በውስጡ የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎችን ይዟል፡፡

1. በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ መፈተሽ፣
2. ይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን በመጨመሩ ረገድ ፋይዳ ካለው የተጽዕኖው መጠን ምን ያህል መሆኑን መመርመር፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ለተመራማሪዎች፣ ለትምህርት መሳሪያ አዘጋጆችና ለመምህራን የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ሊያበረክት ይችላል፡፡

- የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት በቀጥታ ከማስተማር ይልቅ በይዘት ተኮር ዘዴ እንዲያቀርቡ መነሻ ይሆናቸዋል፡፡
- የትምህርት መሳሪያ አዘጋጆች በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር ያለውን ፋይዳ መገንዘብ ስለሚችሉ ለሚያዘጋጁቸው የትምህርት መሳሪያዎች አጋዥ ሊሆናቸው ይችላል፡፡
- ወደፊት በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ጥናታቸውን ማድረግ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች እነደመነሻ ወይም የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግላቸው ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህን ጥናት ትኩረት ያደረገው የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በይዘት ተኮር ዘዴ ማስተማር ለሰዋስው እውቀት መጨመር ያለው ፋይዳ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ለዚህም የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪ ተጠኝዎች ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ይዘት ተኮር ዘዴን በዓረፍተነገር ደረጃ፣ በድስኩር ደረጃና በምንባብ ደረጃ ተመልክቷል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

ጥናቱ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኝ ትምህርት ቤት በመሆኑና ይዘት ተኮር የሰዋስው ትምህርት የሰዋስው እውቀትን የመጨመር ፋይዳ አማርኛን እንደአፍ መፍቻ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ትኩረቱን ያደረገ በመሆኑ በገጠር ዐውድ የሚማሩ ተማሪዎችንና አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን ላይወክል ይችላል፡፡ በተጨማሪም ይዘት ተኮር የሰዋስው ትምህርትን በሚመለከት በአገር ውስጥ የተሰሩ ጥናቶችን ማግኘት አለመቻሉ የጥናቱን ውጤት ከቀደሙ የአገር ውስጥ የጥናት

ውጤቶች ጋር አነጻፅሮ ልዩነቱን ለመመልከት አያስችልም፡፡ በዚህም ጥናቱ መጠነኛ ውስንነት ሊኖርበት ይችላል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ሀረጋት ፍቺ

**የሰዋስው እውቀት፡-** ሰዋስው ስለአንድ ቋንቋ አወቃቀር ሥርዓት ያለን እውቀት የሚያሳይ ሆኖ ከድምጽ አንስቶ እስከ ዓረፍተነገር ያሉትን አሀዶች አካቶ ይይዛል፡፡ ሥርዓቱ ከህብረተሰቡ የቋንቋ አጠቃቀም ጋር አብሮ የሚታይ ነው፡፡ በመሆኑም የሰዋስው እውቀት የሚባለው አንድ ሰው ስለአንድ ቋንቋ ሥርዓትና አጠቃቀም ያለው እውቀትና ግንዛቤ ነው፡፡ በዚህ ጥናትም ተማሪዎች በተመራማሪው በተዘጋጀ የሰዋሰው እውቀት ፈተና ባገኙት ውጤት ተለክቷል፡፡

**ይዘት ተኮር የሰዋስው ትምህርት፡-** ለትምህርት የሚዘጋጀውን የቋንቋ ቅርጽ ለማስተማር፣ ከተማሪዎቹ ፍላጎትና ዳራ ጋር የተዛመደ ጽሑፍ፣ ዲስኩር ወይም ዓረፍተነገር ተመርጦ በትምህርትነት በማቅረብ የሚማሩበት ዘዴ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች

የማስተማሪያ ዘዴ አንድ የቋንቋ መምህር ለማስተማር ያዘጋጃዉን ይዘት እንዴት ቢያስተምር የመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንደሚሆን እና የቋንቋው እውቀት በተማሪዎች አእምሮ እንዴት እንደሚደራጅ የሚያመለክት ሳይንስ ነዉ (Richards and Rodgers, 2001)፡፡ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያየ ስያሜ ማለትም ጥንታዊ እና ዘመናዊ በመባል ይታወቃሉ (Nunan, 1988)፡፡ ከፊሎቹ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ሲሉት ከፊሎቹ ደግሞ መምህር ተኮር እና ተማሪ ተኮር በማለት ይከፍሏቸዋል፡፡ በዚህ ክፍል ክለሳ የተደረገባቸው መምህር ተኮርና ተማሪ ተኮር ዘዴዎች ናቸው፡፡

### 2.1.1 መምህር ተኮር ዘዴ

የማስተማሪያ ዘዴ የስዋስው ይዘትን ለማስተማር ቀደምት ሲጠቀሙበት ቢቆዩም ውጤቱ ግን አመርቂ አይደለም፡፡ መምህር ተኮር ዘዴ ልማዳዊ የትምህርት አሰጣጥ ሲሆን የመማር ማስተማር ሂደቱ በመምህራን የሚጠናቀቅበት ነው (Nunan, 2004)፡፡ በመምህር ተኮር የማስተማር ዘዴ ትግበራ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የሚፈፅሙት ተግባር መናገር እና መፃፍ ብቻ ናቸው፡፡

በመምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንዲያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲመራመሩ፣ እንዲጠያየቁ፣ እንዲመልሱና ሃሳብ እንዲያፈልቁ የሚደረጉበት አጋጣሚ ስለሚያገኙ ትምህርቱን የሚያገኙት አብዛኛውን ጊዜ መምህራን የሚናገሩትን በማዳመጥ እና ማስታወሻ በመያዝ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ፍዝ ተቀባዮች ስለሚሆኑ የመማር ማስተማር ሂደቱ ስልቹ ይሆናል (Richards & Rodgers, 2001)፡፡ መምህር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱን ማዕከል የሚሆኑበት ከመሆኑ የተነሳ የእውቀት ምንጭ ተደርገው የሚታዩበት ነው፡፡ዘዴው መምህር ንቁ ተሳታፊ የሚሆንበት ገለፃ በመስጠት እና በመቆጣጠር

የበላይነት የሚያሳይበት ተማሪዎች ሁል ጊዜ ከግል ስራ ውጭ ምንም ዓይነት ተሳትፎ የማያሳዩበት ስለሆነ ተማሪዎች የተነገራቸውን የሚያዳምጡ ተቀባዮች ይሆናሉ፡፡

### 2.1.2 ዘመናዊ (አሳታፊ) የማስተማሪያ ዘዴ

ዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ስያሜ ይሰጡዋቸዋል፡፡ ትብብራዊ ትምህርት አቀራረብ፣ ራስ የመገንባት አቀራረብ እና አሳታፊ የሚል ስያሜ እንደሰጡት ይገልጻሉ፡፡ የማስተማሪያ ዘዴው መምህራን አንድን የትምህርት ይዘት እንዴት ማስተማር እንዳለባቸዉ እና የመማር ማስተማር ይዘቱ ውጤታማ የሚሆንበት መንገድ የሚመራ ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምሁራን የመምህራንና የተማሪዎች ተሳትፎ መሰረት በማድረግ መምህራን ተኮር እና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በማለት በሁለት ከፍለዋቸዋል፡፡ መምህራን ለሚያስተምሩዋቸዉ ይዘቶች በቂ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፤ እንዲሁም ስለሚያስተምሩት በቂ እዉቀት ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚቆጣጠራቸዉ ትክክለኛ የቋንቋ ሞዴል ማዘጋጀት፣ ተማሪዎችን ማደራጀት፣ ተማሪዎች ያላቸዉን ልምድ እና የሚያደርጉት ሙከራ ለማገዝ አማካሪ መሆን የሚሉት ይገኙባቸዋል (Getachew, 2001):: እንግዲህ ይህን ያህል ካልን የቋንቋ ሰዋስው የማስተማሪያ ዘዴዎች ዉስጥ አንዱ ይዘት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ነዉ፡፡

## 2.2 ይዘት ተኮር አቀራረብ

ቋንቋን ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎችን እንጠቀማለን፡፡ ከእነዚህ የቋንቋ ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች መካከል በቅርብ የተከሰተውና በበርካታ የመስኩ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘው ማቅረቢያ ዘዴ ይዘት ተኮር ነው፡፡ እንደ Met (1999) ገለጻ አቀራረቡ ትኩረት እያገኘ የመጣና በ1980ዎቹ በጥናት ያደገ፣ በዚያው ልክም አገልግሎቱ የሰፋ ነው፡፡ ትኩረት እንዲሰብ ያደረገውም ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ያላቸውን ይዘቶች በማቅረብ ታላሚውን የቋንቋ ትምህርት በማስተማር ላይ ስለሚያተኩርና ጥምር የሆነ አገልግሎት ስላለው ነው (Ngan, 2011)፡፡

### 2.2.1 የይዘት ተኮር አቀራረብ ምንነት

ይዘት የምንለው አካዳሚያዊ ጉዳዮችን (academic/subject matter) ወይም ከትምህርት ውጭ (non academic) የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚያጠቃልል እንደሆነ Hardman (2009,23) ይገልጻሉ። ስለሆነም "ይዘት" በዚህ የቋንቋ ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴ የሚወሰደው የቋንቋን ትምህርት ለማስተማር የሚያገለግል ከተማሪዎቹ ፍላጎትና ባህል ጋር የተጣጣመ ጽሑፍ ነው።

Stephen and Lou (1997) ይዘት ተኮር አቀራረብ የይዘት ትምህርትና የቋንቋ ትምህርት ጥምረት እንደሆነ ያስረዳሉ። የተለያዩ ይዘቶች ይቀርባሉ፤ በቀረቡ ይዘቶች አማካይነት ደግሞ የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎችን ይማራሉ። ሁለቱም በአንድ ላይ ስለሚቀርቡም አቀራረቡ ጥምረታዊ መሆኑን ያስረዳሉ። ይህም የቋንቋ ትምህርትን ለማቅረብ የተለያዩ ምንባቦችን እና እንደመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ድምጽና ድምጽወምስል በመጠቀም ማስተማርን ያጠቃልላል።

ይዘት ተኮር ማለት ቋንቋን ለማስተማር አንዱ ዘዴ ሲሆን ይህም ትኩረት የሚያደርገው በተለያዩ ይዘቶች ላይ በማተኮር እግረ መንገዱን የቋንቋ ክፍሎችን ለማስተማር የሚያገለግል የቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ መንገድ ነው (Hardman, 2009)። በዚህ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ሲማሩ ትኩረት የሚደረገው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ቢሆንም ዋናው ነገር ግን የቋንቋውን ክሂላትና የእውቀት ዘርፎች ለተማሪዎች ማስረጽ መቻል ላይ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች ሙሉ ትኩረት የሚያደርጉት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሲሆን ይህንን ጉዳይ ደግሞ ግልጽ እና ተጨባጭ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ የውይይት ጊዜ ይወስዳሉ። ውይይት አለ ለማለት ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ቋንቋውን ሲጠቀሙ የሰዋስውን ህግ መጠቀማቸዉ አይቀሬ ነው። ይህ ሲደረግ የትምህርት እቅዱ ትኩረት ማድረግ ያለበት በይዘቱ ላይ ነው። ሌሎች የይዘት ክፍሎች ቋንቋ እና የትምህርት ትግበራዎች በተዘዋዋሪ የሚገኙ ናቸው። እነዚህ መተግበር ያለባቸው ይዘቱን መሰረት በማድረግ ነው።

Brinton, Snow and Wesche (1989) እንደሚያስረዱት ይዘት ተኮር አቀራረብ በቋንቋ ትምህርት በተለይም በሰዋስው ትምህርት ጉልህ ሚና እንደሚጫወት ይገልጻሉ። መነሻው የሁለተኛ ቋንቋ እና የውጭ ቋንቋ ተማሪዎችን ለማስተማር ያለመ እንደነበር

ጠቁመው በአፍ መፍቻ ትምህርትም የተማሪዎች የሰዋስው እውቀት አናሳ ሆኖ ሲገኝ ቢተገበር ውጤታማ እንደሚያደርግ ያትታሉ፡፡ Cenoz (2015) በተመሳሳይ በሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር አውድ ቢተገበር እንደአፍመፍቻ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡

በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ቢተገበር የሚመረጥበትን ምክንያት Stephen and Lou (1997) ሲያስረዱ ይዘት ተኮር አቀራረብ እውነተኛውን የቋንቋ አገልግሎ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በቋንቋ ክፍለ ጊዜ የሚተገበር በመሆኑ የቋንቋውን ሥርዓት ጠንቅቆ ለማወቅ ምቹ የሆነ ዘዴ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ Stephen and Lou (1997) ሀሳቡን ሲያብራሩት ዘዴው ተማሪዎች ጥገኛ ሆነው በታላሚው ቋንቋ እንዲማሩ የሚያደርግና በቤታቸውም እንዲተገብሩት የሚያደርግ በመሆኑ የሰዋስው እውቀታቸውንም ሆነ ክሂሎችን ለማዳበር እንደሚያግዛቸው ያስረዳሉ፡፡

ሰዋሰው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንዱ ክፍል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋሰውን ለማስተማር ሲፈለግ በመጀመሪያ ለትምህርት የተዘጋጀውን የቋንቋ ቅርጽ ለማስተማር የሚያገለግልና ከተማሪዎቹ ፍላጎትና ዳራ ጋር የተዛመደ ጽሑፍ ይመረጣል፡፡ ያን ጽሑፍ በትምህርትነት በማቅረብ እግረ መንገዱንም የታለመውን ትምህርት እናስተምራለን፡፡

### 2.2.2 የይዘት ተኮር የማስተማሪያ ስነዘዴ አተገባበር ደረጃዎች

Stephen and Lou (1997) የይዘት ተኮር ዘዴን ለመተግበር ይህ ነው የሚባል ውስን አቀራረብ እንደሌለው በመግለጽ የተለያዩ ትግበራዎችን እንደተማሪዎቹ ባህርይና ዳራ፣ እንደትምህርት ቤቱ ምቹነት እንዲሁም እንደግብዓቱ መለያየት በተለያዩ መንገዶች ሊተገበር እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡

Stephen and Lou (1997) እና Spratt (2016) ይዘት ተኮር የማስተማሪያ አቀራረብ የላይ ታች አቀራረብን (top down approach) መሰረት በማድረግ እንደሚተገበር ያስረዳሉ፡፡ በላይ ታች አቀራረብ መሰረት የቋንቋው ትምህርት ከመቅረቡ በፊት የቀረበላቸውን ውህድ አሀድ በደንብ እንዲረዱት ይደረጋል፡፡ በይዘት ተኮር አቀራረብም እንዲሁ መጀመሪያ ለማስተማሪያነት የሚቀርበው ምንባብ፣ ድስኩር፣ ድምጽ ወይም ድምጽ ወምስል ለተማሪዎች ቀርቦ በደንብ ከተረዱት በኋላ የቋንቋ ክሂሎችንና

እውቀቶችን ይማራሉ፡፡ በመሆኑም የይዘት ተኮር አቀራረብን በክፍል ውስጥ ለማስተማር ተግባራዊ የሚደረጉ ሂደቶች አሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት ቅድመ ትግበራ፣ ጊዜ ትግበራና ድህረ ትግበራ ተግባራት ተብለው ይከፈላሉ፡፡

### 2.2.2.1 ቅድመ ትግበራ

በይዘት ተኮር አቀራረብ ሰዋስውን ለማስተማር ቀድመው መደረግ ያለባቸው ዝግጅቶች ብዙ ናቸው፡፡ ተግባራቱ የሚተገበሩት በአመዛኙ በመምህሩ ወይም በመምህርቷ ነው፡፡ ተግባራቱ ለማስተማሪያ ዘዴው ትግበራ የሚደረጉ ዝግጅቶችንም አብሮ የሚይዝ ነው፡፡ ዝግጅቶቹ ዘዴውን ለመተግበር የሚያግዙ ምንባቦችን ወይም የድምጽና የምስል መረጃዎች የተማሪዎቹ ዳራ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መምረጥና ለትምህርቱ ማስማማት፣ ማስተማሪያ መሳሪያውን መሰረት ያደረገ በትግበራው በተለያዩ ወቅቶች መመለስ ያለባቸውን ጥያቄዎች ማሰናዳት፣ የወንበሮችን አቀማመጥ መምህሩ ወይም መምህርቷ ለመንቀሳቀስ፣ ተማሪዎችንም ለማቀናጀት የሚያመች ማድረግ እና ስለትግበራው ለተማሪዎች በቂ ግንዛቤን መፍጠር ይካተታል (Spratt, 2016)፡፡

የማስተማሪያ ዘዴውን ለመተግበር የሚያግዙ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ሲዘጋጁ መምህሩ ከተማሪዎች ህይወት፣ አካባቢያዊ ዳራ ጋር የተዛመደ፣ የማንበብ ፍላጎታቸውን ሊያነሳሳ የሚችልና ከደረጃቸው ጋር የተመጠጠነ ምንባብ ወይም የድምጽና የምስል ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ Stoller (2002) ያብራራሉ፡፡ የሚዘጋጁ ምንባቦች ታላሚውን የሰዋስው ትምህርት ለማስተማር የሚያግዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በቅድመ ትግበራ ለማድረግ የሚያግዙ ሌሎች ትግበራዎች የመማሪያ ክፍሉን አመችነት ማረጋገጥ፣ የተዘጋጁ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን በበቂ መጠን ማድረስ ይተገበራል፡፡ መምህሩ በይዘቱ ላይ በቂ ዝግጅት ማድረግ እና ለተማሪዎች በሚገባ መንገድ መተግበር መቻልን የሚመለከት ነው፡፡

### 2.2.2.2 ጊዜ ትግበራ

ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ስልትን ተጠቅሞ ሰዋስውን ለመማር ቀደም ብሎ በቅድመ ትግበራ ሊተገበሩ የሚችሉ ተግባራት ከተከናወኑ በኋላ የሚተገበሩ ተግባራትን የሚያካትት ነው፡፡ ተግባራቱም በበቅድመ ትምህርት ስለተዘጋጀው ማስተማሪያ መሳሪያ

ገለጻ መስጠት ከዐውዱ በመነሳት የሚማሩትን ቋንቋ ሰዋስው የሚረዱበትን ዘዴ መጠቆም፣ ተማሪዎችን የቀረበላቸውን ጽሑፍ በጥንቃቄ እንዲያነቡ፣ ካነበቡት ጽሑፍ ውስጥ የተረዱትን የሰዋስው ህግጋት እንዲያወጡና አጠቃቀማቸውን ከዐውዳቸው ለመገመት የሚያስችል ፍንጭ በጽሑፉ ውስጥ መኖሩን እንዲያረጋግጡ መጠየቅና ማዘዝ፣ ካነበቡት ጽሑፍ ወይም ካዳመጡት ድምጽ ውስጥ ያወጧቸውን የሰዋስው ይዘቶች የሚገኙበትን ዐውድ እንደፍንጭ በመጠቀም የቋንቋውን ሥርዓት እንዲገነዘቡት ማድረግ በጊዜ ትግበራ የሚፈጸም ነው (Spratt, 2016)፡፡

መምህሩ ስለማስተማሪያ ዘዴው በቂ ግንዛቤ ካስጨበጠ በኋላ በትምህርቱ መግቢያ የመማር ማስተማር ሂደቱ ሲጀመርም መምህሩ ያለፈውን ትምህርት የሚከልስበት እና የእለቱን ትምህርት ይዘት የሚያስተዋውቅበት ነው፡፡ መምህሩ የእለቱን የትምህርት ይዘት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች ስለ ይዘቱ እንዲናገሩ ያደርጋል፡፡ በትምህርት ጊዜም መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የማስተማሪያ መሳሪያውን አስደምጦ ወይም እንዲያነቡት አድርጎ ይዘቶችን እንዲለዩ ያደርጋል፡፡ የዕለቱ ትምህርት ይዘት ላይ እንዲወያዩ በማድረግ እና ተማሪዎች ሲወያዩ እየዞሩ በመከታተል የመማር ማስተማር ሂደቱን ይመራል፡፡ ከዚያን በኋላ ስለተወያዩበት ርዕሰ ጉዳይ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡፡ እያንዳንዱ ቡድኖችን ካቀረቡ በኋላ መምህሩ ወደ የሚቀጥለው ስራ ይገባል፡፡

በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ለማስተማር በርካታ አጥኚዎች የተለያዩ ማስተማሪያ መንገዶችን ይከተላሉ፡፡ ይህም በሌሎች ትምህርቶች ላይ እንደሚታየው በቡድን ውይይት፣ በግል ሥራ፣ በጥንድ ውይይት ወይም በጥያቄና መልስ ይተገበራሉ፡፡ የቡድን ውይይት ተማሪዎች በቡድን ሆነው እርስ በእርሳቸው ተራክቦ በመፍጠር በተሰጣቸው ይዘት ላይ ሃሳባቸውን በመለዋወጥ፣ በመጠያየቅ፣ በመከራከር ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበት ነው፡፡ የቡድን ስራ አንድን ተግባር ለመስራት ተማሪዎች እርስ በእርስ ሀሳባቸውን፣ እውቀታቸውን፣ አመለካከታቸውን የሚለውጡበት ንቁ ተሳትፎ የሚያሳዩበት፤ መምህሩ በአስተባባሪነት የሚሰራበት ነው (Richards and Rodgers, 2001)፡፡ በተጨማሪም ቋንቋን በተግባቦታዊ ሁኔታ ለማስተማር ከሚረዱ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ሂደቱ ጥገኛ የሚሆነው ተማሪዎች የራሳቸውን ክሂል ተጠቅመው በሚለዋወጧቸው መረጃዎች ላይ ነው፡፡ የቡድን ስራ ተማሪዎች ተሰብስበው ውሳኔ የሚሰጡበት እንዲሁም መምህሩ

ከመምህር ተኮር ማስተማር ዘዴ የሚላቀቅበት ነው (Doff, 1988)፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸው የተሰጣቸውን ተግባር በቡድን በሚደረጉበት ወቅት እድሜን፣ ውጤትን፣ ጓደኝነትን፣ ፍላጎትንና ጾታን መሰረት በማድረግ የቡድን አባለት ማደራጀት ይችላሉ፡፡

ሌላው ተግባራዊ የሚደረገው በግል ስራ ነው፡፡ መምህሩ የትምህርቱ ይዘት ግልጽ እና ተጨባጭ ይሆን ዘንድ ትምህርቱን የግል ስራ በመስጠት ተግባራዊ የሚያደርግበት ዘዴ ነው፡፡ መምህሩ የተለያዩ ይዘቶችን በማዘጋጀት ተማሪዎች ከቤተ-መጽሀፍት አፈላልገው በግል እንዲሰሩ በማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱን አሳታፊ ያደርገዋል፡፡ የግል ስራ አንድ ተማሪ እንዲሰራው የተሰጠውን ነገር ሁሉ ከመምህሩ ብሎም ከጓደኞቹ እገዛ ውጭ ብቻውን የሚሰራበት ነው፡፡ ተማሪዎች የሚሠሩት ነገር ሁሉ ከመምህራን እና ከጓደኞቻቸው ተጽእኖ ነፃ በመሆን በራሳቸው አቅም ስለሆነ በራስ የመተማመን ብቃታቸውን ለመገንባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው (Harmer, 1991)፡፡ ተማሪዎች ለሚሰሩት ነገር በግላቸው ሀላፊነት በመውሰድ የሚሰሩበት ከመሆኑም በላይ የግል እውቀታቸውን ለሌሎች የሚያንጸባርቁበት ነው፡፡ የግል ስራ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በክፍል ስራ መልክ እና በቤታቸው በቤት ስራ መልክ ሊሰጥ ይችላል

ጥንድ ውይይት ደግሞ ተማሪዎች ሁለት ሁለት ሆነው በዕለቱ የትምህርት ይዘት ላይ በመወያየት ትምህርቱን በቀላሉ የሚረዳዱበት እና አይረሴ የሚያደርጉበት ነው፡፡ Doff (1988) በጥንድ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ሁለት ሁለት ሆነው ያልተሟላ ሀሳብ ሲጨርሱ፣ በተሰጠው ርዕሰ ጉዳይ ሲወያዩና በጣም አነስተኛ የሆነ ስራ ሲሰሩ የሚደራጁበት ነው፡፡ አንድ ተማሪ አጠገቡ ካለው ተማሪ ወይም ከአሁን በፊት አብሮት ከአልሰራ ተማሪ ጋር ሊመደብ ይችላል፡፡ ይህ ዘዴ ተማሪዎች በጥንድ ሆነው የተሰጣቸውን ተግባር ከሁለት እስከ ሶስት ደቂቃዎች ባሉት ጊዜታት ከተወያዩ በኋላ ከጥንድ ውይይት ያገኙትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያስተላልፉ የሚደረግበት ነው፡፡ የጥንድ ስራ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ ሆነው የተሰጣቸውን ተግባር በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ እንዲፈፅሙ በማድረግ ከጥንድ ውይይት ያገኙትን ግብአት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያስተላልፉ የሚያደርጉበት ነው፡፡

በጥያቄ እና መልስ የማስተማሪያ ዘዴ ደግሞ ተማሪዎችን በንቃት እንዲሳተፉ ከማድረጉ ባሻገር ትምህርቱን በተዘዋዋሪ መንገድ የማስተላለፊያ ዘዴ ነው (Getachew, 2001)፡፡ ጥያቄ እና መልስ የማስተማሪያ ዘዴ አንድ መምህር አንድን ይዘት ሲያስተምር

ስለሚያስተምረው ርዕሰ ጉዳይ ምን እንደሚያውቁ እና የክፍለ ጊዜው ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ለማድረግ በክፍለ ጊዜው መጀመሪያ ተማሪዎችን በመጠየቅ የሚሳተፉበት ዘዴ ነው። ጥያቄ እና መልስ የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን ማንኛውንም አይነት ጥያቄ ለተማሪዎች በማቅረብ ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ የማድረጊያ ዘዴ ሲሆን ይህም ተማሪዎችን ለማነሳሳት አና መምህራን ለጠየቁት ጥያቄ ለተማሪዎች ምላሽ ለማግኘት ይረዳል።

በጊዜ ትግበራ በመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎች ዋነኛ ሚና ንቁ ተሳታፊ መሆን ነው። ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ደግሞ የተማሪዎች የመማር ፍላጎት ተሳትፎ ተነሳሽነት እና ሌሎች ተጓዳኝ ጉዳዮች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው። ይዘት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ለተማሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል። ጠቀሜታዎቹም ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ያደርጋል፤በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ሲወያዩ ተማሪዎች ቋንቋቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፤የተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜታቸው ይጨምራል፤ በግል የመስራት ስሜትና ግላዊ የስራ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋል፤እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋል፤እርስ በእርስ የመተጋገዝ ባህላቸውን ያዳብራል፤የማህበራዊ መስተጋብራቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛል፤ተማሪዎችች ውስብስብ የሆኑ ክሂሎችን በቀላሉ እንዲማሩ ያደርጋል (Grabe & Stoller, 1997)።

### 2.2.2.3 ድህረ ትግበራ

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ከላይ ወደታች አቀራረብ ጋር ቅርበት ያለው በመሆኑ የሰዋስው ማስተማሪያ ይዘቶችን የሚረዱት ከቀረበላቸው ምንባብ ወይም የድምጽ ግብዓት ነው። በዚያ መሰረት ትምህርቱ ቀርቦ ማወቅ ያለባቸውን የሰዋስው እውቀት በተገቢው መልኩ መረዳታቸውን ለመመርመር ምዝና ማድረግ ተገቢ ነው። ይህም መምህሩ ስለዕለቱ ትምህርት ማጠቃለያ በመስጠት፣ ስለተማሩት ትምህርት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት መረዳት አለመረዳታቸውን በማረጋገጥ የእለቱን ትምህርት የሚጠቃለለው በድህረ ትግበራ ነው። በተጨማሪም እንዳስፈላጊነቱ ቤትወሰድ ተግባራትም እንዲሁ ትምህርቱን ለማጠናከር ሲባል ይካተታሉ።

### 2.2.3 የይዘት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታዎች

ይዘት ተኮር ዘዴ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ፈታኝ ቢሆንም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አቅምን እና ዝግጅትን ቢጠይቅም ለተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ ተነሳሽነት እንዲኖር እና ትምህርቱን በንቃት እንዲከታተሉ ይረዳል፡፡ ትኩረት የሚያደርገውም በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ነው፡፡ ተማሪዎች ፍላጎት ከሌላቸው እየሰበሰቡ መበተን ይሆናል፡፡ ስለዚህ የማስተማሪያ ዘዴው በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ያጠነጠነ ነው፡፡

ስለሆነም የይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ማድረጉ ዋነኛው ጠቀሜታው ነው (Stoller, 2002)፡፡ ትምህርቱ የሚቀርበው በአመዛኙ በተማሪ ተኮር አቀራረብ በመሆኑ በርእስ ጉዳዩ ዙሪያ ሲወያዩ ተማሪዎች ቋንቋን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡ ይህም የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት ይጨምራል፡፡ በግል የሚሰጡ ተግባራትን በሚሰሩበት ወቅት ተማሪዎች በግል የመስራት ስሜት እና ግላዊ የስራ ልምዳቸዉን እንዲያዳብሩ ያደረጋል፡፡ የቋቋውን ሥርዓት ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶችም እንዲሁ ለተማሪዎች ከትምህርት ውጭ ያለውን እዉቀታቸዉን ለማጎልበት ይጠቅማል፡፡ በጥንድና በቡድን እንዲወያዩ በሚደረጉበት ወቅት ደግሞ የእርስ በርስ የመተባበር ልምዳቸዉን ያዳብራል፤ ማህበራዊ መስተጋብራቸዉን እዲያዳብሩ ይረዳል፡፡

በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ሲማሩ ተማሪዎችን ከማበረታታት ባሻገር ትምህርቱ ማራኪ እንዲሆን ሁለት ዋናዋና አስተዋፅዖዎች በይዘት ተኮር ዘዴ ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ደግሞ ተማሪዎች ምንም እንኳን ለመተግበር አስቸጋሪ ቢሆንም ውጤታማነቱ ግን ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች ውስበስብ የሆኑ ክሂሎችን በቀላሉ እንዲማሩ ያደርጋል (Grabe and Stoller, 1997)፡፡ ተማሪዎች በንቃት የሚሳተፉ ከሆኑና እና ፍላጎት ካደረባቸዉ ከይዘቱ ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ይኖራቸዋል፡፡ ይህ ሆነ ማለት ደግሞ ትምህርቱን ሊያስታዉሱትና ሊረዱት ይችላሉ (Ngan, 2011)::

ከዚህ ገለፃ የምንረዳው የይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ምንም እንኳን ለመተግበር ከባድ ቢሆንም ተማሪዎቹ በግል ከመስራት እና ከመምህር ብቻ ከመጠበቅ ይልቅ እርስ በእርስ በመተጋገዝ የግል ብቃታቸውን ማዳበር ከማስቻሉም በላይ የማስተማሪያ ስነ ዘዴው

ተማሪዎች እርስ በእርስ እዲወያዩ ስለሚጋብዝ ቋንቋውን በአግባቡ የመጠቀም ችሎታቸው እንደሚጨምር ያደርጋል፡፡

## 2.3 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ሰዋስውን ለማስተማር ተግባራዊ የሚደረጉ ማስተማሪያ ዘዴዎችን በሚመለከት ውበቱ (2011)፣ ተስፋዬ (2012)፣ ሽፈራው (2013)፣ ፋጡማ (2013) የተለያዩ ምርምሮችን አድርገዋል፡፡

ውበቱ (2011) "ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እና የመጻፍ ክሒል ለማዳበር ያለው ውጤታማነት (በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ምርምር አድርገዋል፡፡ ለምርምሩ ውጤትን መሰረት ባደረገ መልኩ 60 ተማሪዎች በስብጥራዊ የንሞና አመራረጥ ስልት ተካተዋል፡፡ 30 ተማሪዎች ለሙከራ ቡድን 30 ተማሪዎች ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከተደለደሉ በኋላ በቅድመና በድህረ ትምህርት የሰዋስው ፈተናና በመጻፍ ፈተና መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ውጤቱም በገላጭ ስታቲስቲክስ እና በባእድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ የትንተናው ውጤት እንዳመለከተውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ አማካይ ውጤት ማስመዝገባቸውን፣ ጉልህ የሰዋስው እወቀትና የመጻፍ ክሂል ልዩነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም መሰረት ሰዋስውን ከቅርፁ፣ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እና የመጻፍ ክሒል እንደሚያሳድግ አመልክተዋል፡፡

ተስፋዬ (2012) "ሰዋስውን በግልጽ መማር በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም ያለውን ፋይዳ መገምገም"፡፡ በሚል ርዕስ በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ምርምር አድርገዋል፡፡ ለምርምሩም ከ85 ተማሪዎች ከሙከራ ከቁጥጥር ቡድኖች መረጃ ለማሰባሰብ ቅድመና ድህረትምህርት ሰዋስዋዊ ስህተት የመለየትና የማስተካከል ፈተና ተሰጥቷል፡፡ የተሰበሰበው መረጃም በነጻ ናሙና ቲቴስት ስሌት ተተንትኗል፡፡ በትንታኔው መሰረት ሰዋስውን በግልጽ መማር

በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም ያለው ፋይዳ ጉልህ እንደሆነ በጥናቱ አመልክተዋል፡፡

ሽፈራው (2013) “ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ለማሻሻል ያላቸው ሚና፤ በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ምርምር አድርገዋል፡፡ ለምርምሩም በምዕራብ ጎጃም ዞን በደቡብ አቸፈር ወረዳ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል የላሊበላ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ሁለት መማሪያ ክፍል ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ መረጃዎች በፈተናና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ ሲሆን የተሰበሰቡ መረጃዎች በቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋስውን ማስተማር የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና በገላጭ ዘዴ በመጠቀም በድግግሞሽ እና በመቶኛ ውጤቱ ተተንትኗል፡፡ በተጨማሪም አጥኚው በቀጥተኛ ቡድኑ እና በኢቀጥተኛ ቡድኑ የተገኘው የቅድመና ድህረፈተና ውጤት ከ15% ታርሞ ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት በማነፃፀር በነፃ ንሞና ቲ- ቴስት ተተንትኗል፡፡ በምርምሩ ውጤትም ማስተማሪያ ዘዴው የሰዋስው እውቀትንና የመማር ተነሳሽነትን እንደሚያሳድግ አሳይተዋል፡፡

ፋጡማ (2013) “ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙ እና ከአገልግልቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችልታ ማዳበር (በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት)” በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ምርምር አድርገዋል፡፡ ለምርምሩ 30 የሙከራ ቡድንና 30 የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ውጤታቸውን መሰረት ባደረገ መልኩ የተመረጡ ሲሆን ከሁለቱም ቡድን ተማሪዎች መረጃዎች በዳግም ልኬታ ቲቴስት ተተንትነዋል፡፡ በትንታኔው ውጤት ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙ እና ከአገልግሎት ጋር በማቀናጀት ማስተማሪያ ዘዴ ከልማዳዊው የስዋስው ማስተማሪያ ዘዴ የተሻለ ውጤት የሚያስመዘግብ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁሉም ምርምሮች የተለያዩ ሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴዎች የሰዋስውን እውቀትን ከማሳደግ አንጻር ያለውን ፋይዳ መርምረዋል፡፡ በምርምራቸውም ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙ እና ከአገልግልቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማርና ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር እንዲሁም ሰዋስውን በግልጽ መማር የሰዋስው እውቀትን ለማዳበር ጉልህ የሆነ ፋይዳ እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ ሆኖም አጥኚው

ባደረገው የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ በአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ይዘት ተኮር ማስማሪያ ዘዴን በመጠቀም ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለማዳበር ያለውን ፋይዳ በሚመለከት ምርምር ያደረገ ተመራማሪ አልገጠመውም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አኳያ ያለውን ክፍተት ለመሸፈን ሲባል  በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ካሉ ስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ምርምር ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዐውድ በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ ፍትነትመሰል (quasi-experimental) የተሰኘውን ንድፍ ተከትሏል፡፡ በዚህም መሰረት ቅድመና ድሕረትምህርት ባለቁጥጥር ቡድን (quasi-experimental pretest-posttest comparison group) ንድፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የጥናቱ ንድፍ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተገልጿል፡፡

ሰንጠረዥ 1፡- የጥናቱ ንድፍ

| ቡድን | ቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና | በይዘት ተኮር ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ማስተማር | ድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና |
|---|---|---|---|
| የሙከራ | ✓ | ✓ | ✓ |
| የቁጥጥር | ✓ | X | ✓ |

በሰንጠረዥ 1 እንደተመለከተው በጥናቱ ውስጥ የሚሳተፉ ሁለት ቡድኖች ናቸው፡፡ አንደኛው ቡድን የሙከራ ቡድን ሲሆን ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ነው፡፡ ሁለቱም ክፍሎች በእጣ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ ከትምህርቱ በፊት የቅድመ ትምህርት ፈተና ተፈትነው ተመጣጣኝ ውጤት እንዳስመዘገቡ ሲረጋገጥ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን የሚማረባቸው መማሪያ ክፍሎች በእጣ ተለይተዋል፡፡ የሙከራ ቡድኖች ለስምንት ክፍለጊዜ በይዘት ተኮር ዘዴ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ በአንጻሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ የሰዋስው ትምህርትን ለስምንት ክፍለ ጊዜ በመማሪያ መጽሐፉና በመምህር

መምሪያው መሰረት ተምረዋል፡፡ በመጨረሻም የድህረ ትምህርት ፈተና ሁለቱም ቡድኖች ተፍትነዋል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በናሙናነት የተመረጡት ጥናቱ የሚከናወንበት ትምህርት ቤት፣ የክፍል ደረጃ፣ እንዲሁም ተጠኚ ተማሪዎች ናቸው፡፡ እያንዳንዱን ወካዮች ለመምረጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የንሞና ዘዴዎች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ስድስት ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል የቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ አጥኚው በዚሁ ትምህርት ቤት ለበርካታ አመታት በመምህርነት ሙያ አገልግሏል፤ እያገለገልም ይገኛል፡፡ መረጃ ለማግኘት ካለማስቸገሩና ስለተማሪዎቹ አጠቃይ መረጃ ለማግኘት የተጠቀሰው ትምህርት ቤት ተመራጭ በመሆኑ በአመቺ የንሞና ስልት በጥናቱ ተካቷል፡፡

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በቃሊቲ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋሰውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ ለመፈተሽ ጥናቱ ሲከናወን ተጠኝ ሆነው የተመረጡት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ይህ የክፍል ደረጃ የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ለተከታታይ ዓመታት ሲያተምር በአስረኛ ክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ዝቅተኛ ሆኖ ያገኘው በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የክፍል ደረጃ በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡

### 3.2.3 የተማሪዎች አመራረጥ

በጥናቱ ላይ ተሳታፊ የሆኑት በ2016 ዓ.ም. በቃሊቲ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ የክፍል ደረጃ ሲማሩ የነበሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲማሩባቸው የነበሩ አምስት መማሪያ ክፍሎች ሲሆኑ በአምስቱም መማሪያ ክፍሎች 281 ተማሪዎች አሉ፡፡ የሙከራ ጥናቱን ለማጥናት

ይመች ዘንድ ከአምስቱ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ክፍሎች ቀላል የእጣ ናሙና ስልትን በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡ ክፍሎች 10B እና 10E ናቸው፡፡ አንዱ ክፍል ደግሞ ለሙከራ ጥናት (Pilot Study) ደግሞ 10A ተመርጧል፡፡ ለዋናው ጥናት የተመረጡ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብዛት ከ10B 48 ተማሪዎች ከ10E ደግሞ 47 ተማሪዎች (በድምሩ 95 ተማሪዎች) ተመድበዋል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በጠቅላይ የንሞና ስልት የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

የጥናቱን ዓላማ ግብ ለመምታት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ፈተና ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ፈተናው የተዘጋጀው የክፍል ደረጃውን መርሃ ትምህርት መሰረት በማድረግ ያደረገ ሆኖ የተዘጋጁት ጥያቄዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ አወቃቀርን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የፈተና ይዘቶች በዓረፍተነገር ክፍሎች (ባለቤት፣ ተሳቢ፣ ማሰሪያ አንቀጽ)፣ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚታዩ የተለያዩ ስምምነቶች (የቁጥር፣ የጾታ፣ የጊዜ፣ የመደብ)፣ የቃላት ቅድም ተከተላዊ አቀነጃጀት፣ በቃል ክፍሎችና በሐረጎች ዙሪያ የሚያጠነጥኑና ስነፍቺን መሰረት ያደረጉ 20 ጥያቄዎች ናቸው፡፡

የተዘጋጀው ፈተና በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ሁለት ጊዜ ተሰጥቷል፡፡ በቅድመ ትምህርት ወቅት የተሰጠው ፈተና ዓላማ በጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የተማሪዎቹን የሰዋስው እውቀት ዳራ ተመጣጣኝ እንደነበር ለመፈተሽ ነው፡፡ የድህረ ትምህርቱ ፈተና ዓላማ ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በተለመደው ማስተማሪያ ዘዴ እንዲሁም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ከተማሩ በኋላ ስነዘዴው በተማሪዎች የሰዋስው እውቀት መሻሻል ላይ የሚያሳድረውን አስተዋጽኦ ለመርመር እንዲሁም የተጽኖውን መጠን ለመፈተሽ አገልግሏል፡፡

የቅድመና የድህረትምህርት ፈተናው ለታለመለት ዓላማ ከማገልገሉ በፊት በጥናቱ አማካሪ፣ በቋንቋ መምህራን አስተያየት ተሰጥቶታል፡፡ ከዚያም የፈተናውን አስተማማኝነት ለመፈተሽ በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ በሚማሩ ተማሪዎች የሙከራ ጥናት (pilot study) ተካሂዶበታል፡፡ በሙከራ ጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች ቁጥር 25 ሲሆን ፈተናውን ተፈትነው ያገኙት ውጤት በCronbach's Alpha ቀመር ተሰልቷል፡፡

በስሌሉቱ መሰረት ውጤቱም $\alpha = .789$ ሆኗል (የፈተናውን አስተማማኝነት ለመለካት ያገለገለው መረጃ በአባሪ 2 ላይ፣ ስሌቱ አባሪ 7 ላይ ተመልክቷል)፡፡ ይህም መረጃ ለመሰብሰብ አስተማማኝ በመሆኑ ፈተናውን ለዋናው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ እንዲያገለግል ተደርጓል፡፡

## 3.4 የጥናቱ ሂደት

በመጀመሪያ በጥናቱ ላይ አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ አካላት (ተጠኚ ተማሪዎች፣ የትምህርት ቤቱ አስተዳደርና መምህራን) ፍቃድ ተጠይቆ የምርምሩን ዓላማ በማስረዳት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በዚህ መሰረት የተመረጡ ናሙና ተማሪዎች ከክፍል ደረጃቸው ጋር የተዘጋጀላቸውን ተመጣጣኝ ጥያቄዎች ሰርተዋል፤ ቅድመ ትምህርት ፈተናውን ከወሰዱ በኋላ፣ ትምህርቱ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ትምህርቱ በናሙናነት ከተመረጡ ተማሪዎች ጋር በመስማማት በሳምንት ሁለት ጊዜ ለአራት ተከታታይ ሳምንታት ተሰጥቷል፡፡ በእርግጥ ለጥናቱ ለሁለት ወር ቢሰጥ ተመራጭ እንደሆነ ይታመናል፤ ሆኖም ግን ካለው የጊዜ መጣበብ አንጻር በአንድ ወር ትምርቱ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በትምህርቱ ላይ የተቀረጸው የሰዋስው ይዘት የክፍል ደረጃውን መርሃ ትምህርት መሰረት ባደረገ መልኩ በይዘት ተኮር ዘዴ በአጥኚ መምህሩ ተዘጋጅቷል፡፡

ፈተናዎቹም ሆኑ ትምህርቶቹ የተሰጡት አንደኛው ክፍለ ጊዜ ከትምህርት ፈረቃቸው ውጪ አንደኛውን ክፍለ ጊዜ ደግሞ በመማሪያ ክፍላቸው ነው፡፡ በመጨረሻም ድህረ ትምህርት ፈተናን ተፈትነዋል፡፡ የፈተና ወረቀቶቹ በአጥኚው ከታረሙ በኋላ ውጤቶቹ በጥንቃቄ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ (ኮድ ሽት) ላይ ተመዝግበዋል፡፡ በአጥኚው የታረመበት ምክንያት ጥያቄዎቹ ቁርጠኛ ምላሽ የላቸው በመሆናቸውና ግላዊ አመለካከትን የሚጠይቁ ባለመሆናቸው ነው፡፡ ለማረም በመስፈርትነት ያገለገለውም በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡበት መንገድ ነው፡፡

## 3.5 የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት

የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍና የመምህር መምሪያ ተምረዋል፡፡ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ግን የማስተማሪያ ማኑዋል ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ የማስተማሪያ ማኑዋሉ ይዘቶች የተካተቱት ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መማሪያ

መጽሐፍ እና ከመርሀ ትምህርቱ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት ለክፍል ደረጃቸው የሚመጥን ይዘት የሚገኘው ከመማሪያ መጽሐፉና ከመርሀ ትምህርቱ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚያም ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የሚመለከቱ ከተዳሰሱ ንድፈሀሳባዊ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የማስተማሪያ ማኑዋሉ ተዘጋጅቷል፡፡

በይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በቅድመ ትግበራ፣ በትግበራ ጊዜማ በድህረ ትግበራ የሚከናወኑ ተግባራት በማስተማሪያ ማኑዋሉ ላይ ተካተው ተዘጋጅተዋል፡፡ በቅድመትምህርት ትግበራ ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የሚያመች የተለያዩ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን በክለሳ ድርሳናት ላይ ተገልጿል፡፡ በዚህ ጥናት ከመማሪያ ክፍሉ ሁኔታና ከቁሳቁሶች አቅርቦት አንጻር ተግባራዊ የተደረገው ምንባብንና ዲስኩርን መጠቀም ነው፡፡ ስለሆነም የክፍል ደረጃቸውን የሚመጥኑና የማስተማሪያ ዘዴውን ለመተግበር የሚያግዙ ምንባቦች፣ ምልልሶችና ዓረፍተነገሮች ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም በማስተማሪያ መሳሪያው አማካይነት የሰዋስው ይዘቶችንና አጠቃቀማቸውን እንዲለዩ የሚያደርጉ ተግባራትም ተካተው ቀርበዋል፡፡ በተዘጋጀው ማኑዋል አማካይነት የተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ በጥንድና በቡድን ውይይት፣ በግል ሥራዎች፣ በቤት ወሰድ (የቤት) ሥራዎችና በመሳሰሉት ትምህርቱ ቀርቧል፡፡

## 3.6 የመረጃ ትንተና ዘዴ

ፈተናው በአጥኚው ታርሞና ውጤቱ ተመዝግቦ የነጻ ናሙና ቲቴስትና የCohen’s d (Cohen’s d) ስሌቶች አማይነት ተተንትነዋል፡፡ የነጻ ናሙና ቲቴስት በቅድመና በድህረትምህርት በሙከራና በቁጥጥር ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር እንዲሁም Cohen’s d ነጻ ተላውጦው በጥገኛ ተላውጦዎች ላይ ያስገኘውን የተጽእኖ መጠን ለማስላት አገልግሏል፡፡ በመሆኑም በፈተናዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልትን በመከተል ተተንትነዋል፡፡

ከትንታኔው አስቀድሞ ስለሰዋስው እውቀት የተመዘገቡ ውጤቶች ውስጥ ፍንግጥ ነጥቦች አለመኖራቸው በባለሳጥን ግራፍ ተሰርተው ፍንግጥ ነጥቦች እንደሌሉ ተረጋግጧል (የባለሣጥን ግራፎችን ከአባሪ 12 እና ከአባሪ 13 ላይ ይመልከቱ)፡፡ በኋላም የነጻ ናሙና ዋና እሙን የሆነውን የውጤቶች መደበኛ ሥርጭት መሟላቱን በተደጋጋፊ

አምድ ግራፎችና በሻፒሮ ዊልክ አማካይነት ፍተሻ ተደርጓል፡፡ ከአባሪ 8 እና 9 ላይ እንደተመላከተው የተገኙ የሻፒሮ ዊልክ ውጤቶች ከ0.05 በላይ (P > 0.05) በመሆናቸው መደበኛ ስርጭቱን ያሟሉ እንደሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የተደጋጋፊ አምድ ግራፉ እንደሚያሳየው የተመዘገቡ ውጤቶች አንጻራዊ የሆነ የሥርጭት ወጥነት እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

መረጃዎቹ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት መሰረታዊ እሙን የሆነውን የስርጭት ወጥነት አሟልተው እንደተገኙ በተገለጸው መንገድ ከተፈተሸ በኋላ በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኖች የቅድመትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከልና በሁለቱ ቡድኖች የድህረትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለማወቅ ሲባል መረጃዎች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡ ነጻ ተላውጦው (ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ) በጥገኛ ተላውጦው (የሰዋስው እውቀት) ላይ ያስገኙትን የተጽእኖ መጠን (effect size) በCohen’s d ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና የትንታኔው ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ቀዳሚ ጥያቄ "በይዘት ተኮር ዘዴ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?" የሚል ነው፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ሲባልም ፍትነቱ በሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከመተግበሩ በፊት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎችና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከሰዋስው እውቀት አንጻር ተመጣጣኝ መሆን አለመሆናቸውን ለመፈተሽ አንድ አይነት የቅድመትምህርት የሰዋስው እውቀት መለያ ፈተና ተፈትነው ውጤታቸው ተመዝግቧል (የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት ፈተና ውጤቶችን ከአባሪ 3 እና 4 ላይ ይመልከቱ)፡፡ በቅድመትምህርት የሰዋስው እውቀት ፈተና ከሁለቱ ቡድኖች የተገኙት መረጃዎች በነጻ ናሙና ቲቴስት ተፈትሸው የተገኙት ውጤቶች በሰንጠረዥ 2 ላይ ተገልጿል፡፡

ሰንጠረዥ 2፦ የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙና (n) | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር | 48 | 12.125 | 2.523 | -0.670 | 93 | 0.505 |
| የሙከራ | 47 | 12.532 | 3.348 | | | |

በሰንጠረዥ 2 ላይ እንደተገለጸው በቅድመትምህርቱ የሰዋስው ፈተና አማካይ ውጤት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ውጤት ጋር ሲነጻጸር በ0.407 በልጦ ተገኝቷል፡፡ በመደበኛ ልይይትም በተመሳሳይ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር በ0.825 በልጠዋል፡፡ ይህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የታየው የሰዋስው ፈተና ውጤት ልዩነት ስታትስቲክሳዊ ጉልህነት ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመፈተሽ ሲባል መረጃዎቹ በነጻ ናሙና ቲቴስት ተፈትሸዋል፤ የተገኘው ውጤትም $t(93) = -0.670$, $p = .505$ ነው፡፡ በቲቴስት

ፍተሻው በተገኘው ውጤት መሰረት በቁጥጥር ቡድን ተማዎችና በሙከራ ቡድን ተማሪዎች የሰዋስው ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ስታትስቲክሳዊ ልዩነት የላቸውም፡፡ በዚህም ሙከራው ከመካሄዱ በፊት ሁለቱ የጥናቱ ተሳታፊ ቡድኖች በሰዋስው እውቀት ተመጣጣኝ እንደነበሩ መረዳት ተችሏል፡፡

የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የሰዋስው አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ውጤት ከሙከራው አስቀድሞ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ተመጣጣኝ እንደነበሩ በሰንጠረዥ 2 ላይ በተገለጸው መሰረት ተረጋግጦ የሙከራ ትግበራው ተተግብሯል፡፡ ከትግበራው በኋላ ሁለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ የድህረትምህርት የሰዋስው እውቀት ፈተና ተፈትነው በውጤቶቻቸው መካከል ያለው ልዩነት በነጻ ናሙና ቲቴስት ተፈትሿል፤ የቲቴስት ውጤቱም በሰንጠረዥ 3 ተገልጿል፡፡ (የሁለቱ ቡድኖች የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች ከአባሪ 5 እና ከአባሪ 6 ላይ ይመልከቱ)፡፡

ሰንጠረዥ 3፡- የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙና (n) | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር | 48 | 12.563 | 2.492 | -3.462 | 93 | 0.001 |
| የሙከራ | 47 | 14.404 | 2.692 | | | |

ሰንጠረዥ 3 እንደተገለጸው ከአማካይ ውጤት አንጻር የሙከራ ቡድን ተሳታፊዎች ከቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች በ1.841 ይበልጣሉ፡፡ በመደበኛ ልይይትም በተመሳሳይ የሙከራ ቡድን ተሳታፊዎች ከቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች በ0.2 ይበልጣሉ፡፡ በእርግጥም ልዩነታቸው ስታተስቲካዊ ጉልህ መሆኑን ለመፈተሽ በሁለቱ ቡድን ተሳታፊዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተፈትሿል፡፡ የተገኘው ውጤትም $t(93) = -3.462$, $P = 0.001$ ነው፤ ውጤቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የፍትነቱ ቡድን በልጦ ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡

ይህም የቁጥጥር ቡድኑ ተሳታፊዎች ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው የተማሪ መጽሀፍ እና የመምህር መምሪያ መሰረት፣ የሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ደግሞ በይዘት ተኮር

የሰዋስው ትምህርት አማካይነት ሰዋስውን ተምረው ሙከራው እንደተጠናቀቀ፤ የሙከራ ቡድን ተሳታፊዎች ከቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች በአማካይ ውጤታቸው በልጠው በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት ማሳየታቸውን ያመለክታል። ለዚህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ለታየው የሰዋስው እውቀት ውጤት ልዩነት ምክንያቱ የሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ሰዋስውን በይዘት ተኮር ዘዴ አማካይነት መማራቸው እንደሆነ መረዳት ተችሏል።

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ "ይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን በመጨመሩ ረገድ ፋይዳ ካለው የተጽዕኖው መጠን ምን ያህል ነው?" የሚል ነው። በጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ የተገኘው ውጤት ይዘት ተኮር የሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የሰዋስው እውቀት ላይ ለውጥ አምጥቷል። ሆኖም ግን የቲቴስት ውጤቱ ለውጥ እንዳመጣ እንጂ የለውጡ መጠን ምን ያህል እንደሆነ አይጠቁምም። ለዚህም ተጨማሪ ፍተሻ አስፈልጓል።

ይዘት ተኮር ዘዴ በተማሪዎች የሰዋስው ችሎታ ላይ ያሳደረውን የተጽእኖ መጠን ለመፈተሽ አገልግሎት ላይ የዋለው የCohen's d ቀመር ነው። በፍተሻውም ውጤቱም d = 0.71 ሆኗል። ይህም ይዘት ተኮር ዘዴ በተማሪዎች የሰዋስው ችሎታ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለው የሚያሳይ ነው።

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዐውድ በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ መፈተሽ ነበር። ለፍተሻውም የተተኳሪ ተማሪዎችን የሰዋስው እውቀታቸውን ለመለካት በተዘጋጀው የሰዋስው ፈተና ተሰብስቦ የነጻ ናሙና ቲቴስትና የCohen's d ስሌቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል።

የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ "በይዘት ተኮር ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?" የሚል ሲሆን በሰዋስው ፈተናዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የነጻ ናሙና ቲቴትስ ትንተና ተደርጓል። በትንተናው ውጤት መሰረት ($t(93) = -3.462$, $P = 0.001$) ነው።

ውጤት $P<0.05$ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት እንዳለ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ከሙከራው (ከትምህርቱ) በኋላ ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ በመሆኑ ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የሰዋስው እውቀትን ከማሳደግ አንጻር የጎላ ፋይዳ እንዳለው ተረጋግጧል፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት Hardman (2009) ይዘት ተኮር ዘዴን ተጠቅሞ ሰዋስውን ማስተማር ለሰዋስው እውቀት ጉልህ ሚና እንዳለው ከገለጹት ሀሳብ ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት ይሁን (2013) እና ሽፈራው (2013) ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ ተስፋዬ (2012) ሰዋስውን በግልጽ መማር በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም ያለውን ፋይዳ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ ውበቱ (2011) ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እና የመጻፍ ክሒል ለማዳበር ያለው ውጤታማነት በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ካጠኑት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የተጠቀሱት ጥናቶች ሰዋሰውን ለማስተማር የተጠቀሙባቸው ብልሀቶች ለሰዋስው እውቀት መጨመር ፋይዳ እንዳላቸው የገለጹ ሲሆን የፋይዳቸው መጠን ግን የተለያዩ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይህም ሰዋስውን ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎችን እንዳስፈላጊነቱና እንደምናስተምረው ይዘት ባህርይ እየቀያየርን መጠቀም የሚኖረውን ፋይዳ የሚጠቁም ነው፡፡

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ “ይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን በመጨመሩ ረገድ ፋይዳ ካለው የተጽዕኖው መጠን ምን ያህል ነው?” የሚል ነው፡፡ የተጽዕኖውን መጠን ለማጥናት በፈተናዎቹ የተገኙ አማካዮችን፣ መደበኛ ልይይቶችንና የናሙና መጠኖችን በመጠቀም የCohen’s d ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በፍተሻውም ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የሰዋስው እውቀትን ከማሳደግ አንጻር ያለው ፋይዳ ጠንካራ እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሱት ጥናቶች ከተጠቀሙባቸው ዘዴዎች የተሻለ ተጽዕኖ እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት Grabe and Stoller (1997) ይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የሰዋስው እውቀትን ከመጨመር አንጻር ያለውን ፋይዳ ከገለጹት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ፋጡማ (2013) ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙ እና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችሎታ ከማዳበር አንጻር ያለውን ፋይዳ መርምረው ጠንካራ ፋይዳ እንዳለው ከገለጹት የጥናት ውጤት ጋር የሚቀራብ ግኝት ተገኝቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዐውድ በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ መፈተሽ ነው። በውስጡ የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎችን ይዟል።

1. በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ መፈተሽ፣
2. ይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን በመጨመሩ ረገድ ፋይዳ ካለው የተጽዕኖው መጠን ምን ያህል መሆኑን መመርመር።

የተጠቀሱ ንዑሳን ዓላማዎችን ለመመለስ መረጃዎች በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ከሚገኙ ስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን አመቺ የንሞና ዘዴን በመጠቀም ተመርጧል። በትምህርት ቤቱ በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋሰውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ ለመፈተሽ ጥናቱ ሲከናወን ተጠኝ ሆነው የተመረጡት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ የተመረጡትም በአመቺ የንሞና ስልት ነው። በ2016 ዓ.ም የ10ኛ ክፍል ደረጃን ከሚማሩ አምስት መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 2 መማሪያ ክፍሎች (10B እና 10E) በቀላል የእጣ ንሞና ስልት ተመርጠዋል። በናሙናነት በተመረጡ እያንዳንዳቸው ክፍሎች ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ 51 ነበሩ። ሆኖም ግን በተለያዩ ምክንያቶች የቀሩና በጥናቱ ያልተሳተፉ 7 ተማሪዎች (ከቁጥጥር ቡድን 3፣ ከሙከራ ቡድን 4 ተማሪዎች) በጥናቱ ሳይሳተፉ ቀርተዋል። በመሆኑም የጥናቱ ተሳታፊዎች ለቁጥጥር ቡድን 48፣ ለሙከራ ቡድን 47፣ በድምሩ 95 ተማሪዎች ናቸው።

ከ95 ተማሪዎች በቅድመና ድህረትምህርት መረጃዎች የተሰበሰቡት በሰዋስው ፈተናዎች አማካይነት ነው። ፈተናዎች በአጥኚው የተዘጋጁ ሲሆን ወደዋናው ተጠኚ ተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰቢያነት ከማገልገላቸው በፊት በጥናቱ አማካሪና በትምህርት ቤቱ

በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገምግመዋል፡፡ አስፈላጊ ማሻሻያዎች ከተደረጉ በኋላም በጥናቱ ባልተሳተፉ 25 ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት ተደርጓል፡፡ በሙከራ ጥናቱ የተገኙ መረጃዎች የCronbach's Alpha ስሌት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ከ0.7 በላይ በመሆኑ የፈተናው አስተማማኝነት ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በቅድመና በድህረትምህርት መረጃ ለመሰብሰቢያነት አገልግሏል፡፡

ከፍትነቱ በፊት ሁለቱም ቡድን ተማሪዎች ፈተናውን ተፈትነው በተገኘው ውጤት አማካይነት ተመጣጣኝ ውጤት እንደነበራቸው በነጻ ናሙና ቲቴስት ፍተሻ ተፈትሿል፡፡ ከዚያም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉና በመምህር መምሪያ ባለው የሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴ አማካይነት፣ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ደግሞ በይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ አማካይነት የሰዋስው ትምህርትን ተምረዋል፡፡ በመጨረሻም የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በሰዋስው ፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ከተመዘገቡ በኋላ በነጻ ናሙና ቲቴስት ተሰልቷል፡፡

በትንታኔው መሰረት ከአማካይ ውጤት አንጻር የሙከራ ቡድን ተሳታፊዎች ከቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች የላቀ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ የውጤት ልዩነታቸው ስታተስቲካዊ ጉልህ መሆኑን ለመፈተሽ በሁለቱ ቡድን ተሳታፊዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር የፍትነቱ ቡድን በልጦ ጉልህ ልዩነት (t(93) = -3.462, P = 0.001) መኖሩን አመላክቷል፡፡

ይዘት ተኮር ዘዴ የሰዋስው እውቀትን ከማሳደግ አንጻር ያለውን የተጽዕኖ መጠን ለመፈተሽ በተደረገው የCohen's d ፍተሻ ከፍተኛ ተጽኖ እንዳለው (d = 0.71) የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዐውድ በይዘት ተኮር ዘዴ ሰዋስውን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለመጨመር ያለውን ፋይዳ መፈተሽ ነው፡፡ በፍተሻው መሰረት ከጥናቱ የትንታኔ ውጤት በመነሳት የሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

1. ይዘት ተኮር ዘዴን ተጠቅሞ የሰዋስው ትምህርትን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ከማዳበር አንጻር ጉልህ የሆነ አስተዋጽኦ ያበረክታል።
2. ይዘት ተኮር ዘዴን ተጠቅሞ የሰዋስው ትምህርትን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ለማዳበር ያለው የተጽዕኖ መጠን ጠንካራ ነው።

## 5.3 አስተያየት

የዚህ ጥናት አጥኚ ከጥናቱ ግኝት በመነሳት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አስተያየቶችና የጥናት ጥቆማ አቅርቧል።

1. በጥናቱ ግኝት እንደቀረበው ይዘት ተኮር ዘዴን ተጠቅሞ የሰዋስው ትምህርትን ማስተማር የሰዋስው እውቀትን ከማዳበር አንጻር ጉልህ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። ይህ የሆነበት ምክንያትም የቁጥጥር ቡድኑ ተሳታፊዎች ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው የተማሪ መጽሀፍ እና የመምህር መምሪያ መሰረት፣ የሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ደግሞ በይዘት ተኮር ዘዴ አማካይነት በመማራቸው ነው። በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ለማዳበር ይዘት ተኮር ዘዴን ቢተገብሩ፤
2. ይዘት ተኮር ዘዴ አተገባበር ከተለመደው የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ለየት ባለ አቀራረብ የሚቀርብ ነው። በመሆኑም በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወይም ማሻሻል ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች የሰዋስው ትምህርትን አቀራረብና ማስተማሪያ ዘዴ ሲያዘጋጁ ለይዘት ተኮር ዘዴ ትግበራ ምቹ የሆኑ አቀራረቦችንና ማስተማሪያ ዘዴዎችን ቢያካትቱ፤
3. ይህ ጥናት የተደረገው አማርኛን እንደአፍመፍቻ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ነው። በሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ምርምር ማድረግ የሚፈልጉ ተመራማሪዎች አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ምርምር ቢያደርጉ።

## ዋቢ ጽሑፎች

ሙሉጌታ ይታየው። (1996)። *የተማሪ ተኮር ማተማሪያ ዘዴ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮተቤ መምህራን ትምህረት ኮሌጅ የሰርተፊኬት መርሃ ግብር እንደታየው።* አማርኛን በመማር ስነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አዲስ አበባ።

ሽፈራው አቅናው። (2013)። *ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ለማሻሻል ያላቸው ሚና፤ በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት።* አማርኛን በማስተር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፤ ጎንደር።

ባየ ይማም። (2000)። *የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ የት.መ.ማ.ማ.ድ.።

ተስፋዬ ለገሰ። (2012)። *ሰዋስውን በግልጽ መማር በአረፍተነገር ምስረታ ሂደት የሚፈጠሩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመለየትና ለማረም ያለውን ፋይዳ መገምገም፡* አማርኛን በማስተር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤ ደብረ ብርሃን።

አዲስዓለም ዘሪሁን። (2012)። *የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በሚጽፉት ድርሰት ላይ የሚስተዋሉ አሉታዊ የሰዋስው ተጽዕኖዎች እና የግድፈት ምንጮች ፍተሻ።* አማርኛን በመማር ስነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት። ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ ባሕር ዳር።

አሚናት መሀመድ። (2016)። *በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት (በእኖር ኤነር መገር ወረዳ የመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት)።* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አዲስ አበባ።

ይሁን ተስፋዬ። (2013)። *ሰዋስውን በቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ዘዴዎች ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀትና ሰዋስውን የመማር ተነሳሽነት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት።* አማርኛን በማስተር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፤ ጎንደር።

ዮሐንስ አያሌው፡፡ (2003)፡፡ *"የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሁኔታ የአተገባበር ግምገማ (በሰሜንወሎ ዞን በሚገኙ ሁለት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች)፡፡* አማርኛን በመማር ስነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አዲስ አበባ፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ (1990)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡* አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ውበቱ በዛብህ፡፡ (2011)፡፡ *ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እና የመጻፍ ክሒል ለማዳበር ያለው ውጤታማነት (በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)፡፡* አማርኛን በማስተር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤ ደብረ ብርሃን፡፡

ፋጡማ ጀዋድ፡፡ (2013)፡፡ *ሰዋስውን ከቅርፁ፣ ከትርጉሙ እና ከአገልግልቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችልታ ማዳበር (በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት)፡፡* አማርኛን በማስተር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፤ ጅማ፡፡

Anne, S. (2007). *Basic English Grammare For English Language Learners*. USA፡ Saddleback Education Publisher.

Atkins, J., Hailom, B. and Nuru, M. (1995). *Skill Development Methodology*. Addis Ababa: A.A.U. Press.

Brinton, D. M., Snow, M. A., & Wesche, M. B. (1989). *Content-based second language instruction.* New York: Newbury House.

Brown, D. (1994). *Principle of Language Learning and Teaching*. USA: Prentice Hall.

Bygate, M., Alan, T. and Eddie, W. (1994). *Grammar and Language Teacher.* Hempstead Printice Hall.

Carter, R. (1990). *Knowledge About Language And The Curriculum*. Hadder sought London.

Cenoz, J. (2015). Content-Based Instruction and Content and Language Integrated Learning: The Same or Different?. *Language, Culture and Curriculum,* 28 (1), 8-24.

Celce-Murcia, M. (1991). *Teaching English as a Second or Foreign Language.* Boston: Heinlein and Heinlein Publishers.

Cunningsworth, A. (1995). *Choosing Your Course Book.* Oxford: Heinemann.

Doff, A. (1988). *Teach English: A Training Course for Teachers*. Cambridge: Cambridge University Press.

Getachew, A. (2001). Three Modules In The Teaching of Secondary School Amharigna Subject. Area Methodology Department of Curriculum. Fuculity of Education. AAU. unpublished.

Grabe, W. & Stoller, F. L. (1997). Content Based Instruction: Research Foundation. In M.A> snow, and D.M. Brinton (ed). The Content Based Class Room: Perspective on Integrating Languages and Content. (PP.5-21). Longman.

Hardman, M. C. (2009). “Developing A Teachers’ Handbook for Content based Instruction at Brigham Young University’s English Language Center”. in partial fulfillment of the requirements for the degree of Master of Arts. Brigham Young University. (Unpublished).

Harmer, I. (1978). *Teaching and Learning Grammar*. Hong ong. london.

Harmer, J. (1991). *The Principle of English Language Teaching*. London: Longman Group UK Limited.

Met, M. (1999). *Content-based instruction: Defining terms, making decisions.* NFLC Reports. Washington, DC: The National Foreign Language Center.

Miros, O. (2004). “On The Effectiveness of Options In Grammar Teaching.” From: http://www.thefreeLiabrary.Com

Ngan, N. T. (2011). *Content-based Instruction in the Teaching of English for Accounting at Vietnamese College of Finance and Customs*. Canada: Canadian Center of Science and Education.

Nunan, D (1988). *The Learner Centered Curriculum*. Cambridge. Cambridge University press.

Nunan, D. (2004). *Language teaching methodology: Textbook for teachers*. Malaysia: Longman.

Richards, J., & Rodgers, T. (2001). Approaches and Methods in *Language Teaching*. New York: Cambridge University Press.

Salimun, M. (2008). “Goods and Techniques For Teaching Grammar” on Line; http;/www.Ask.com

Snow,M.A.(2001). Content Based and Immersion Module for Second and Foreign Language Teaching.

Spratt, M. (2016). Focus on Content-Based Language Teaching, *ELT Journal,* 70 (4), 476—478.

Stephen B. S. & Lou, L. B. (1997). *Content-based instruction in foreign language education: models and methods*. Georgetown University Press.

Stern. H.H (1992) *Grammar Practice Activities*: *Apractical Guide For Teachers.* Cambridge: Cambridge university press.

Stoller, F. (2002). Promoting the acquisition of knowledge in a content based course. In J. Crandall & D. Kaufman (Eds.), Content-based instruction in higher education settings (pp. 109—123). Alexandria, VA: TESOL.

Stoller, S. (2006). Establishing a Theoretical Foundation for Project Based Learning In second and Foreign Language Context. *Foreign languages Education:* pass, present, future pp.19- 40 Green which.

Ur, P. (1988). *Grammar Practice Activity Approach Guide For Teachers*. Cambridge. Cambridge university press.

Ur, P. (2006). A Course in Language Teaching practice and theory. (13th edition). Cambridge: Cambridge University Press.

Widodo, H. (2006) "Approach and Procedures for Teaching Grammar". From: http//aducation.waikato,ac.a2/files/etpc/2006v.sn1.Ppt

# አባሪዎች

## አባሪ1፡- ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና

በይዘት ተኮር የማስተማሪያ ስነዘዴ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና (20%)

*መለያ ኮድ፡-*____________________ ፈተናው የሚጀመርበት ሰዓት፡- 1፡00

ለፈተናው የተፈቀደ ጊዜ፡- 1፡00 ሰዓት

የጥያቄዎች ብዛት፡- 20

**አጠቃላይ *መመሪያ*፤** ይህ ፈተና በቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይዘት ተኮር የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ለሰዋስው ትምህርት ያለውን ፋይዳ ለመፈተሽ እየተካሄደ ላለው ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተዘጋጀ ነው፡፡ የፈተናው ሁሉም ጥያቄዎች በምርጫ ስልት የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የአንተ (የአንቺ) የሰዋስው እውቀት አስፈላጊ ስለሆነ በመመሪያው መሰረት ፈተናውን በመስራት የበኩልህን (የበኩልሽን) አስተዋጽኦ እንድታበረክት (እንድታበረክች) እጠይቃለሁ፡፡ የፈተናው ውጤት በምስጢር ይያዛል፡፡

በየክፍሎቹ ለቀረቡ ጥያቄዎች ሌሎች ንዑሳን መመሪያዎች የተዘጋጁ ሲሆን እንደየንዑሳን ክፍሎች መመሪያ አጠያየቅ ተገቢውን መልስ ስጥ(ጭ)፡፡

**ማሳሰቢያ**፤ *ፈተናውን ከመጀመርህ/ሽ አስቀድሞ የፈተናው ገጾች ብዛት ሶስት መሆናቸውን አረጋግጥ(ጭ)፡፡*

**መመሪያ፡- በዚህ ፈተና ሰዋስውን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ይሆናሉ ተብለው ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን ምረጥ/ ምረጪ፡፡**

______1.ከሚከተሉት ቃላት አንዱ በስም የቃል ክፍል ይመደባል፡፡

ሀ.ደግ ሐ.ገና

ለ.በላ መ.ፈረስ

______2. በሀረግ ውስጥ አይቀሬው ክፍል የትኛው ነው?

ሀ. አጎላማሽ ሐ. መሙያ

ለ. ገላጭ መ. መሪ

______3. ከሚከተሉት ውስጥ ለየት ያለ የሀረግ አይነት የቱ ነው?

ሀ. እንደእህቷ መሰሪ ሐ. እጅግ ትልቅ

ለ. በጣም ጥቁር መ. እንደወንድሙ ቶሎ

______4. የቃል ክፍሉ ስም የሆነ ቃል ሊሆን የማይችለው የቱ ነው?

ሀ. ባለቤት ሐ. ተሳቢ

ለ. ማሰሪያ አንቀፅ መ. የነገሮች ወይም የቁሶች መጠሪያ

______5. “ጠጣ” የሚለው ቃል “ግስ” መሆኑን የምንለየው __________ በማመላከቱ ነው፡፡

ሀ. ሁነት ሐ. ድርጊት

ለ. ባህሪ መ. ስያሜ

______6. የሚከተለውን ምልልስ በትኩረት በማንበብ በምልልሱ ውስጥ ከስሩ የተሰመረበት በየትኛው የቃል ክፍል እንደሚጠቃለል ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡

ሳራ፡- ልጅሽ ተሻለው?

አለሚቱ፡- ምን ባክሽ **ክፉኛ** ታሟል፡፡

ሳራ፡- አይዞሽ ይድናል፤ ብቻ የአንች ክትትል አይለየው፡፡

ሀ. በስም ሐ. በተውሳከግስ

ለ. በግስ መ. በቅጽል

________7. ከቃል ክፍሎች ለቃላት እርባታም ሆነ ምስረታ የማይውለው የትኛው ነው?

ሀ.ግስ ሐ. ስም

ለ.መስተዋድድ መ. ቅጽል

________8. ከዚህ በታች የተለያዩ ሀረጋት ተዘርዝረዋል፡፡ ከስራቸው ከተሰመረባቸው **በግስ** የቃል ክፍል የሚጠቃለለው የቱ ነው?

ሀ.አጭር ሰው ሐ.ከእህቱ ጋር

ለ.ጥቁር በሬ መ.ወደቤቱ ሄደ

________9. በአንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ድርጊቱን የፈጸመው ወይም የሆነውን አካል የሚያመለክተው __________ ተብሎ ይጠራል፡፡

ሀ. ባለቤት ሐ. ማሰሪያ አንቀጽ

ለ. ተሳቢ መ. ግስ

_______10. "________ውሻ ያለበት ግቢ በሌባ አይደፈርም፡፡" ዓረፍተነገሩን የሚያሟላው ቃል የተ ነው?

ሀ. ተናካሽ ሐ. ቀይ

ለ. ድንክ መ. አመለኛ

______11. "የሰጠሽን" በሚለው ቃል ውስጥ የሌለ ቅጥያ የቱ ነው?

ሀ. -ን ሐ. -ኧ

ለ. -ኧሽ መ. -ሽ

________12. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ነጠላ (ተራ) ዓ.ነገር የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ዛሬ የበላሁት ምሳ ስላልተስማማኝ ሆዴን አመመኝ፡፡

ለ. ወደ ቤቱ ዘሎ ገባ፡፡

ሐ. ዛሬ ከእህቱ ጋር ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

መ. ቶሎ ደርሰህ ተመለስ፡፡

______13. ስለምዕላድ ልክ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ወደአነስተኛ ትርጉም ሰጪ አሀዶች መከፈል ይችላል፡፡

ለ. ራሱን ችሎ ሊቆምም ላይቆምም ይችላል፡፡

ሐ. ሁሉም ምዕላዶች እንደቃላት ቅጥያ ያስጨምራሉ፡፡

መ. ቅጥያዎች በጥገኛ ምዕላድ ምድብ ይካተታሉ፡፡

______14. የምስረታ ምዕላድ እና የእርባታ ምዕላድ ያለው ቃል የትኛው ነው?

ሀ. ልጆቻችን ሐ. የድንበርህን

ለ. ኢትዮጵያዊውን መ. የነገርኩህን

______15. "አያት" የሚለው ቃል "ተመለከታት" የሚል ፍቺ የሚኖረው በየትኛው ንበት ነው?

ሀ. "ያ" ሲጠብቅ ሐ. "ት" ሲጠብቅ

ለ. "ያ" ሲላላ መ. "ት" ሲላላ

________16. "እየሄደ ኤፍሬም ወደ ትምህርት ቤት ነው፡፡" የሚለው ተዘበራርቆ የቀረበው ዓረፍተ ነገር ሲቃና

ሀ. ኤፍሬም እየሄደ ወደትምህርት ቤት ነው፡፡

ለ. ወደትምህርት ቤት ኤፍሬም እየሄደ ነው፡፡

ሐ. ኤፍሬም ወደትምህርት ቤት እየሄደ ነው፡፡

መ. ወደትምህርት ቤት እየሄደ ኤፍሬም ነው፡፡

______17. "በጣም ______ ልጅ ዛሬ ተሳካለት፡፡" በክፍት ቦታው ሊገባ የሚችል የቃል ክፍል የትኛው ነው?

ሀ. ስም ሐ. ተውሳከግስ

ለ. ግስ መ. ቅጽል

______18. "ሰበረ" ብለን "አሰባበረ" ካልን "ሰበሰበ" ብለን ምን እንላለን?

ሀ. አስሰበሰበ ሐ. ሰባሰበ

ለ. አሰባሰበ መ. አሰበሰብን

______19. "ጥልቅ እውቀት ያለው ሰው አንደበቱ ቁጥብ ነው፡፡" የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. የተለያየ ሐ. ውስን

ለ. ርቀት ያለው መ. ብዙ

______20. "ዓይን" የሚለው ቃል በእማሬያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው ዓረፍተነገር ነው?

ሀ. ልጂቱ የቤተሰቡ ዓይን ናት፡፡ ሐ. ጎላ ጎላ ያለ ዓይን አላት፡፡

ለ. የባትሪው ዐይን ተቃጠለ መ. ዓይን ያወጣ ውሸት ዋሸች፡፡

## አባሪ 2፦ የሰዋስው ፈተናውን አስተማማኝነት ለመፈተሽ የተሰበሰበ መረጃ

| መለያ ኮድ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | ድምር |
| 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **17** |
| 2 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | **8** |
| 3 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **13** |
| 4 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **11** |
| 5 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | **9** |
| 6 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **16** |
| 7 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **14** |
| 8 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | **15** |
| 9 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | **12** |
| 10 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **19** |
| 11 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | **10** |
| 12 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **11** |
| 13 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **20** |
| 14 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **11** |
| 15 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | **13** |
| 16 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | **8** |
| 17 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **10** |
| 18 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **18** |
| 19 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | **7** |
| 20 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **20** |
| 21 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | **8** |
| 22 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **16** |
| 23 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **18** |
| 24 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | **8** |
| 25 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **14** |

## አባሪ 3:- የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤት

| መለያ ኮድ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | **ድምር** |
| 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | **13** |
| 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | **8** |
| 3 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **18** |
| 4 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **7** |
| 5 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | **9** |
| 6 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | **11** |
| 7 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | **12** |
| 8 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | **11** |
| 9 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | **12** |
| 10 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **11** |
| 11 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | **11** |
| 12 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **14** |
| 13 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | **8** |
| 14 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **14** |
| 15 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | **9** |
| 16 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **14** |
| 17 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | **13** |
| 18 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **12** |
| 19 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **12** |
| 20 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **11** |
| 21 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | **10** |
| 22 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **15** |
| 23 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **14** |
| 24 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | **10** |
| 25 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **13** |
| 26 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | **11** |
| 27 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | **11** |
| 28 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **17** |
| 29 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **12** |
| 30 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **14** |
| 31 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **13** |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | **12** |
| 33 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | **12** |
| 34 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | **12** |
| 35 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **15** |
| 36 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **13** |
| 37 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **17** |
| 38 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | **8** |
| 39 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **14** |
| 40 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | **9** |
| 41 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | **11** |
| 42 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **12** |
| 43 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **14** |
| 44 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **13** |
| 45 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **18** |
| 46 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **9** |
| 47 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **11** |
| 48 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | **12** |

### አባሪ 4:- የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤት

| መለያ ኮድ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | **ድምር** |
| 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **12** |
| 2 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | **8** |
| 3 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | **11** |
| 4 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **8** |
| 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **19** |
| 6 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | **14** |
| 7 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | **12** |
| 8 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | **7** |
| 9 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | **9** |
| 10 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | **11** |
| 11 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **15** |
| 12 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **11** |
| 13 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **13** |
| 14 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **13** |
| 15 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **14** |
| 16 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | **15** |
| 17 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | **11** |
| 18 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | **13** |
| 19 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | **13** |
| 20 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | **8** |
| 21 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | **8** |
| 22 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **17** |
| 23 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **14** |
| 24 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **14** |
| 25 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | **14** |
| 26 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | **12** |
| 27 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **17** |
| 28 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | **7** |
| 29 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **18** |
| 30 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **13** |
| 31 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **14** |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | **12** |
| 33 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | **9** |
| 34 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | **10** |
| 35 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | **14** |
| 36 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **17** |
| 37 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **16** |
| 38 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **17** |
| 39 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | **8** |
| 40 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | **11** |
| 41 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | **14** |
| 42 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | **7** |
| 43 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **17** |
| 44 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **12** |
| 45 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | **8** |
| 46 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **13** |
| 47 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **19** |

## አባሪ 5:- የቁጥጥር ቡድኑ የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤት

| መለያ ኮድ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | ድምር |
| 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | **9** |
| 2 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **10** |
| 3 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **18** |
| 4 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | **8** |
| 5 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **16** |
| 6 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | **12** |
| 7 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | **12** |
| 8 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | **12** |
| 9 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | **9** |
| 10 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | **13** |
| 11 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **11** |
| 12 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **15** |
| 13 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | **15** |
| 14 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **18** |
| 15 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | **10** |
| 16 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | **14** |
| 17 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | **12** |
| 18 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **13** |
| 19 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | **14** |
| 20 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **11** |
| 21 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | **12** |
| 22 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | **11** |
| 23 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **10** |
| 24 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **17** |
| 25 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **12** |
| 26 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | **13** |
| 27 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | **13** |
| 28 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **16** |
| 29 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **15** |
| 30 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | **14** |
| 31 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | **14** |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | **11** |
| 33 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **13** |
| 34 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | **10** |
| 35 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | **12** |
| 36 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **13** |
| 37 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | **13** |
| 38 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | **10** |
| 39 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **13** |
| 40 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | **8** |
| 41 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **13** |
| 42 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **11** |
| 43 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **14** |
| 44 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | **12** |
| 45 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **18** |
| 46 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **11** |
| 47 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | **9** |
| 48 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | **13** |

## አባሪ 6:- የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤት

| መለያ ኮድ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | ድምር |
| 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | **10** |
| 2 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | **14** |
| 3 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **14** |
| 4 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | **11** |
| 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **19** |
| 6 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **15** |
| 7 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **14** |
| 8 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | **12** |
| 9 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | **14** |
| 10 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **15** |
| 11 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **16** |
| 12 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **14** |
| 13 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **16** |
| 14 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **12** |
| 15 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **15** |
| 16 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | **16** |
| 17 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **13** |
| 18 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **14** |
| 19 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **15** |
| 20 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **14** |
| 21 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **9** |
| 22 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **20** |
| 23 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **17** |
| 24 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **15** |
| 25 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **16** |
| 26 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **14** |
| 27 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | **15** |
| 28 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | **9** |
| 29 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **19** |
| 30 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **17** |
| 31 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **15** |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | **15** |
| 33 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | **10** |
| 34 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **13** |
| 35 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **16** |
| 36 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | **17** |
| 37 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **19** |
| 38 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | **15** |
| 39 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **9** |
| 40 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | **13** |
| 41 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **14** |
| 42 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **13** |
| 43 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **18** |
| 44 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | **15** |
| 45 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | **11** |
| 46 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | **12** |
| 47 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **18** |

## አባሪ 7፦- የሰዋስው ፈተናው አስተማማኝነት ፍተሻ ስሌት በCronbach’s Alpha

**Reliability Statistics**

| Cronbach's Alpha | Cronbach's Alpha Based on Standardized Items | N of Items |
|---|---|---|
| .789 | .791 | 20 |

**Item Statistics**

| | Mean | Std. Deviation | N |
|---|---|---|---|
| Question01 | .9200 | .27689 | 25 |
| Question02 | .6800 | .47610 | 25 |
| Question03 | .8400 | .37417 | 25 |
| Question04 | .7200 | .45826 | 25 |
| Question05 | .6000 | .50000 | 25 |
| Question06 | .6000 | .50000 | 25 |
| Question07 | .6400 | .48990 | 25 |
| Question08 | .7200 | .45826 | 25 |
| Question09 | .5600 | .50662 | 25 |
| Question10 | .4000 | .50000 | 25 |
| Question11 | .3200 | .47610 | 25 |
| Question12 | .7200 | .45826 | 25 |
| Question13 | .4400 | .50662 | 25 |
| Question14 | .7200 | .45826 | 25 |
| Question15 | .6000 | .50000 | 25 |
| Question16 | .6800 | .47610 | 25 |
| Question17 | .7600 | .43589 | 25 |
| Question18 | .6400 | .48990 | 25 |
| Question19 | .9200 | .27689 | 25 |
| Question20 | .5600 | .50662 | 25 |

**Item-Total Statistics**

| | Scale Mean if Item Deleted | Scale Variance if Item Deleted | Corrected Item-Total Correlation | Cronbach's Alpha if Item Deleted |
|---|---|---|---|---|
| Question01 | 12.1200 | 16.277 | .270 | .785 |
| Question02 | 12.3600 | 15.907 | .217 | .788 |
| Question03 | 12.2000 | 15.667 | .388 | .778 |
| Question04 | 12.3200 | 15.560 | .328 | .781 |
| Question05 | 12.4400 | 14.423 | .601 | .763 |
| Question06 | 12.4400 | 15.673 | .261 | .786 |
| Question07 | 12.4000 | 16.083 | .161 | .792 |
| Question08 | 12.3200 | 14.810 | .549 | .767 |
| Question09 | 12.4800 | 15.760 | .234 | .788 |
| Question10 | 12.6400 | 15.240 | .376 | .778 |
| Question11 | 12.7200 | 14.710 | .553 | .767 |
| Question12 | 12.3200 | 15.477 | .352 | .780 |
| Question13 | 12.6000 | 14.250 | .641 | .760 |
| Question14 | 12.3200 | 15.060 | .474 | .772 |
| Question15 | 12.4400 | 16.340 | .091 | .797 |
| Question16 | 12.3600 | 15.240 | .401 | .777 |
| Question17 | 12.2800 | 15.793 | .281 | .784 |
| Question18 | 12.4000 | 15.000 | .452 | .773 |
| Question19 | 12.1200 | 16.193 | .308 | .783 |
| Question20 | 12.4800 | 16.010 | .170 | .792 |

አባሪ 8፡- የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ በሻፒሮ-ዊልክ

| የመደበኛ ሥርጭት ፍተሻ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቡድን | ኮልሞጎሮቭ-ስሚርኖቭ[a] | | | ሻፒሮ-ዊልክ | | |
| | | ስታትስቲክ (Statistic) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (Sig.) | ስታትስቲክ (Statistic) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (Sig.) |
| የቅድመትምህርት ፈተና | የቁጥጥር | .116 | 47 | .125 | .963 | 47 | .140 |
| | የሙከራ | .104 | 47 | .200* | .955 | 47 | .070 |
| a. Lilliefors Significance Correction | | | | | | | |

አባሪ 9፡- የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የድህረትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ በሻፒሮ-ዊልክ

| የመደበኛ ሥርጭት ፍተሻ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቡድን | ኮልሞጎሮቭ-ስሚርኖቭ[a] | | | ሻፒሮ-ዊልክ | | |
| | | ስታትስቲክ (Statistic) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (Sig.) | ስታትስቲክ (Statistic) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (Sig.) |
| የድህረትምህርት ፈተና | የቁጥጥር | .132 | 47 | .040 | .962 | 47 | .126 |
| | የሙከራ | .142 | 47 | .018 | .965 | 47 | .165 |
| a. Lilliefors Significance Correction | | | | | | | |

አባሪ 10፦ የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ በተደጋጋሬ አምድ ግራፍ

የቁጥጥር ቡድኑ




የሙከራ ቡድኑ



**አባሪ 11፡- የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርት የሰዋስው ፈተና ውጤቶች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ በተደጋጋሬ አምድ ግራፍ**

**የቁጥጥር ቡድኑ**




**የሙከራ ቡድን**



አባሪ 12፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤቶች የፍንግጥ ውጤቶች መኖር አለመኖር ፍተሻ በባለሳጥን ግራፍ

የቁጥጥር ቡድን




የሙከራ ቡድን



**አባሪ 13፡- የድህረትምህርት ፈተና ውጤቶች የፍንግጥ ውጤቶች መኖር አለመኖር ፍተሸ በባለሳጥን ግራፍ**

የቁጥጥር ቡድን




የሙከራ ቡድን



## አባሪ 14፡- የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ሰዋስውን በዐውድ ተኮር ለማሰልጠን የሚያገለግል ማሰልጠኛ ማኑዋል

### *መግቢያ*

ይዘት ተኮር የሰዋስው ትምህርት ሰዋስውን ለማስተማር በቀጥታ የቋንቋ ይዘቶችን ከማቅረብ ይልቅ ይዘቶችን እውናዊ በሆነ የቋንቋ ተግባቦት ውስጥ በማስገባት የሚቀርብበት ዘዴ ነው፡፡ በተለይም በምንባቦች በዲስኩሮችና በመሳሰሉት ውስጥ አስገብቶ መማር ነው፡፡ በምናነበው ጽሑፍ ወይም በምናዳምጠው ንግግር ውስጥ የሚገጥሙንን የቋንቋ ሥርዓቶች የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የምንረዳበትና ሌላ ጊዜ አስታውሰን መጠቀም እንድንችል ደግሞ በሌላ ዐውድ የምንጠቀምበት አቀራረብ ነው፡፡ እዚህ ላይ ያሉ ሁለት ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1. የሰዋስው ይዘቶችን ከገቡበት ምንባብ ወይም ዲስኩር አንጻር መረዳት እና
2. የተረዳናቸውን የሰዋስው ይዘቶች በሌላ ዐውድ መጠቀም የሚሉት ናቸው፡፡

### የዐረፍተነገር ዓይነቶች

ይዘቱ የሚቀርበው፡- በምንባብ፣ በዓረፍነገር፣ በትግበራና በድስኩር

ዐረፍተነገርን በዓይነት ለመክፈል የሚያስችሉ የተለያዩ መስፈርቶች አሉ፡፡ እነርሱም፤ አገልግሎት፣ አወቃቀር እና ሥነጽሑፋዊ ጠቀሜታ ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል የምንመለከተው የዐረፍተነገር ዓይነቶችን ከአገልግሎትና ከመዋቅር አንጻር ይሆናል፡፡

ተግባር

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በጥሞና በማንበብ ተመሳሳይ ከአገልግሎታቸው አንጻር ቅርጽ ያላቸውን ዓረፍተነገሮች በምድብ በምድብ አስቀምጡ፡፡

"ቤርሳ . . . ቤህ"

" አስመዝግቤሻለሁ ታነቢያለሽ"

*ቃሉን በጭራሽ አላመነችም !ክውብላ ደነገጠች፡፡ እንደምንም ቃላትን ፈልጋ ግን ተነፈሰች፡፡ "እየቀለድክ መሆን አለበት?"*

“ ሕይወት ራስዋ ቀልድ አይደለችም? … ለማንኛውም ከምሬ ነው ታነቢያለሽ”

“አልችልም ያ ሁሉ ህዝብ ፊት ቆሜ … አልችልም”

“ አስረኛ ክፍል ስታስተምሪን አንድ የማልረሳው አባባል ነግረሽኝ ነበር፡፡ እምነት ካለህ የማይቻል ምንም ነገር በምድር ላይ የለም ፤ ብቻ ልብን ማሳመን ነው” ይህን መቼም አልረሳውም፤ በራስዋ ቃል እስረኛ ሆነች፡፡ ምንም ስላልነበራት ፈገግ እያለች እንደተስማማች ነገረችው፡፡ አመስግኖ ስልኩን ዘጋው፡፡

“እጅግ ጥሩ ጓደኛህ ውስጥህ ያለውን መልካም ነገር እንድታወጣው ይደርግሃል፤ ያበረታታሀል፣ ደካማጎንህን ይነግርሀል፤ ይመክርሀል ጥሩ ጎኑን ላንተ ያስተምርሃል … ይህን መሰል ጓደኛ በዓለም ላይ የሚያገኙት የተወሰኑት ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡”

ከአባቱዋ ያልጨረሱት መፅሐፍ ላይ ያነበበችው ነው፡፡ አቤንኤዘር ለሷ ጥሩ ጋደኛዋ እንደሆነ አሰበች፡፡ በጣም ስታስብ ደሞ ከዚያ በላይም እንደሆነ ተረዳች፡፡ ሕይወቷን ለትንሽ ደቂቃ ቃኘች፡፡ ዳግማዊ፣ አቤንኤዘር፣ አባትዋ፣መኪያ … ሕይወት እሽክሪክሪት ብዛት ካላቸው ሰዎች ጋር ተገኝታለች፡፡ ከሁሉም ትላንት ተማሪዋ ስለ ነበረው ዛሬ ጓደኛዋ ስለሆነው አቤንኤዘር ስታስብ ግን እጅግ ግርም ይላታል፡፡ ያመነችው ነገር ምናልባት ከእርሱ ጋር ባትገናኝ ኖሮ እድሜ ልኩዋን ግጥምን በማድነቅ ብቻ ትኖር እንደ ነበር ገመተች፡፡

“ቀጥሎ ግጥሙዋን የምታቀርብላችሁ ቤርሳቤህ ናት” ገና ወደ መድረክ ስትወጣ አብዛኛው አዳራሻ ውስጥ የነበረው ወጣት በውበትዋ በጣሙን ተደነቁ፡፡ የእነርሱ እንድትሆንም ተመኙ፡፡

መጠነኛ ፍርሀት ቢንፀባረቅባትም ወደ መድረኩ ቀርባ ማይኩን ስትይዘው ፍርሀቱ እየቀነሰላት መጣ፡፡ ራስዋን አረጋጋች፡፡ የነፃነት እስረኛ የሚለውን አንብባ ከመጨረሱዋ ደመቅ ያለ ጭብጨባ ተከተላት፡፡ አመስግና ጭብጨባው ጋብ ሲል ሁለተኛውን ግጥም አነበበች፡፡

(ምንጭ ፡- የሆነው ነገር ይሰማኛል፣ ገፅ 114 ሀ 115 ያልታተመ፣ አዘርግ)

ተማሪዎች የመደባችኋቸውን ዓረፍተነገሮች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩባቸው፡፡ ውይይቱ ተገቢውን ምደባ መከተል አለመከተላችሁን መሰረት ያደረገ ይሁን፡፡

መልካም አሁን የተወያያችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራችሁን ጠብቃችሁ ተናገሩ፡፡

ተማሪዎች!!! ከእናንተ መካከል ፈቃደኛ የሆኑ አራት ተማሪዎች እፈልጋለሁ፡፡ (መምህሩ አራት እጃቸውን ያወጡ ተማሪዎችን አስወጥተው ከተማሪዎች ፊት ለፊት እንዲቆሙ ያደርጋሉ፤ ለእያንዳንዱ ተማሪዎች የሚሰሩትን ተግባር ያስረዳሉ)

ተማሪ አንድ  ተማሪ ሁለትን መጠየቅ የምትፈልገውን ነገር ጠይቀው፡፡ ተማሪ ሁለት ደግሞ ተማሪ አንድ ለጠየቀህ ጥያቄ ምላሽ ስጥ፡፡ ተማሪ ሶስት ተማሪ አራትን እንዲያደርግል የምትፈልገውን ነገር እዘዘው፤ ተማሪ አራት ደግሞ የማይሆን ነገር ካዘዘህ ትዕዛዙን በደስታ መቀበልህን፤ በትዕዛዙ ከተናደድክ ደግሞ ንዴትህን ግለጽለት፡፡ ሁላችሁን ሀሳባችሁን የምትገልጹት በተሟላ ዓረፍተነገር ይሁን (ተማሪዎችም የታዘዙትን ያደርጋሉ)

ተማሪዎች!! የተማሪዎችን ምልልስ በሚገባ አጤናችሁ? መልካም!!! አሁን በተመሳሳይ አራት ፍቃደኛ የሆኑ ተማሪዎች እፈልጋለሁ፡፡ እፈልጋለሁ፡፡ (መምህሩ አራት እጃቸውን ያወጡ ተማሪዎችን አስወጥተው ከተማሪዎች ፊት ለፊት እንዲቆሙ ያደርጋሉ፤ ለእያንዳንዱ ተማሪዎች የሚሰሩትን ተግባር ያስረዳሉ፡፡) ተማሪ አምስትን ከተማሪ አንድ ጎን፣ ተማሪ ስድስትን ከተማሪ ሁለት ጎን፣ ተማሪ ሰባትን ከተማሪ ሶስት  ጎን እንዲሁም ተማሪ ስምንትን ከተማሪ አራት ጎን እንዲቆሙ ያደርጋሉ፡፡ የታዘዙት ተግባር ተማሪዎቹ የመሰረቷቸውን ዓረፍተነገሮች ባለመስማማት (በአሉታ ቅርጽ) እንዲገልጹ ነው፡፡ ተማሪዎቹ የታዘዙትን ተግባር ይተገብራሉ፡፡

ተማሪዎች የታዘዛችኋቸውን ተግባራት በታዘዛችሁበት መልኩ ሰርታችኋል፡፡ ተማሪዎች እስካሁን ከተደረጉት ምልልሶች ምን ተረዳችሁ? ስለዓረፍተነገር አይነቶችስ ምን ግንዛቤ ጨበጣችሁ፡፡ ጎበዞች!!! እንደገለጻችሁት በጽሑፋዊም ሆነ በቃላዊ ተግባቦት የተለያዩ ሚናዎች አሏቸው፡፡ ሚናዎቹም ጥያቄን መጠየቅ፣ ትዕዛዝን ማዘዝ፣ ሀሳብን ማብራራት ወይም መግለጽ እንዲሁም የተለያዩ ስሜቶችን ማንጸባረቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም እንዳዳመጣችሁት በአሉታና በአዎንታ ቅርጽ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በመሆኑም ተማሪ

አንድና ተማሪ አምስት ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር፣ ተማሪ ሁለትና ተማሪ ስድስት ሀተታዊ ዓረፍተነገር፣ ተማሪ ሶስትና ተማሪ ሰባት ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገር እንዲሁም ተማሪ አራትና ስምንት አጋናኝ ዓረፍተ ነገሮችን እንደመሰረቱ መረዳት ችላችኋል፡፡

ስለተለያዩ ጉዳዮች ስንናገር ወይም ስንጽፍ የተለያዩ ዐረፍተነገሮችን እንጠቀማለን፡፡ ዐረፍተነገሮች እንደሚነገሩበት ዓላማና ተግባር የተለያዩ በመሆናቸው ከአገልግሎታቸው አንጻር ሐተታዊ፣ መጠይቃዊ፣ ትዕዛዛዊ እና አጋናኝ ተብለው በዐራት ይከፈላሉ፡፡ ሐተታዊ ዐረፍተነገር፣ አንዳች ሁነትን፣ ድርጊትን ወይም ኑረትን የሚገልጽ የዐረፍተነገር ዓይነት ነው፡፡ የሚገለጸው ነገርም አካላዊ ወይም ረቂቅ ሊሆን ይችላል፡፡ የዐረፍተነገሩ ተግባር መንገር፣ መግለጽ ወይም ማተት ነው፡፡ ሀተታው አሉታ ወይም አዎንታ ከመሆኑ ባሻገር፣ አጠቃላይነት ወይም ውሱንነት ስላለው ባሕርይ እንዲሁም ርዕሰጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡

ምሳሌ፣ ሀ. አየሩ ሞቃታማ ነው፡፡

ለ. ተማሪዎች ትምህርት ቤት ተገኝተዋል፡፡

ሐ. እህቴ ዛሬ ሥራ አልሄደችም፡፡

መጠይቃዊ ዐረፍተነገር፣ በአንድ ዐረፍተነገር ውስጥ ስለአንድ ነገር ወይም ጉዳይ ለማወቅ፣ መረጃ ለማግኘት ወይም ለማረጋገጥ አገልግሎት ላይ የሚውል የዐረፍተነገር ዓይነት ነው፡፡ ዐረፍተነገሩ መጠይቃዊ ተውላጠ ስሞችን (ማን፣ ምን፣ የት፣ ስንት፣ መቼ፣ እንዴት ወዘተ.) ወይም መጠይቃዊ ተውላጠ ስሞችን ከመስተዋድዶች ጋር በማቀናጀት (ለምን፣ በምን፣ ከየት፣ ከማን፣ ወደየት ወዘተ.) እና ትእምርተጥያቄን በመጠቀም ሊቀርብ ይችላል፡፡

ምሳሌ፣ ሀ. ለምን አታነብም?

ለ. መቼ መጣሽ?

ትዕዛዛዊ ዐረፍተነገር፣ የትዕዛዝ ተግባር ያለው የዐረፍተነገር ዓይነት ሲሆን፣
ትዕዛዙ በተለያየ መንገድ (በአስገዳጅ እና አስገደዳጅ ባልሆነ መልኩ) እንደዐውዱ ተለያይቶ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜ ትእዛዝ በሚሰጠውና ትዕዛዝ በሚቀበለው ሰው መካከል ያለው የመግባባት ደረጃ ወይም ወሰን የትዕዛዙን አቀራረብ ይወስነዋል፡፡ ትዕዛዝ

ተቀባዩ በግልጽ ከታወቀ፣ ትዕዛዝ በሦስተኛ ወገን ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊቀርብ ይችላል።

ምሳሌ፣ ሀ. በሩን ዝጋው። (ደረቅ ትዕዛዝ፣ አስገዳጅ)

ለ. እባክሽ በሩን ዝጊው። (በልመና ወይም በትህትና የቀረበ ትዕዛዝ፣ አስገዳጅ ያልሆነ)

ሐ. ጋሻው ላሚቱን ይጠብቅ። (በተዘዋዋሪ በሦስተኛ ወገን የቀረበ)

አጋናኝ ዐረፍተነገር፣ ከስሜት ጋር የተያያዙ ሐሳቦች የሚገለጹበት የዐረፍተነገር ዓይነት ነው። ከውስጣችን የሚወጣ ኃይለኛ ስሜትን (መገረምን፣ መደነቅን፣ መደንገጥ፣ መቆጣትን፣ ደስታን፣ ሐዘንን ወዘተ.) ይገልጻል።

ምሳሌ፣ ሀ. ውይ! ነገሩ በጣም ያስገርማል። (መገረምን)

ለ. ዋው! ጫካው እንዴት ያምራል። (መደነቅን)

በገለጻው መሰረት የሚከተሉት ተግባራት ተግብሩ።

፩. የሚከተሉትን ዐረፍተነገሮች ከአገልግሎታቸው አንጻር በዓይነታቸው ለዩ።

1. የቤት ሥራውን ሰራህ እንዴ?
2. ፐ! ግሩም ጎል ነው።
3. ዶክተር ሰብለ ጎበዝ መምህር ናት።
4. ተነስና መስኮቱን ዝጋ።
5. ከሰዓት በኋላ ወደቢሮ አልገባም።

፪. እስካሁን የነበሩትን ትግበራ መሰረት በማድረግ አራት አባላት ያሉት ቡድኖች በመመስረት የዓረፍተነገር አይነቶችን ከአገልግሎት አንጻር የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮችን በምልልስ መልኩ መስርቱ።

ተማሪዎች የተሰጧችሁን ተግባራት በተገቢው መልኩ በመስራታችሁ ኮርቸባችኋለሁ፤ እናንተም ልትኮሩ ይገባል። ከተገበራችኋቸው ተግባራት ዓረፍተነገሮችን ከገልግሎት አንጻር እንዴት ማዋቀር እንዳለባችሁ ተረድታችኋል።

ተግባር

መመሪያ፡- የሚከተሉትን ምልልሶች በመረዳት ከምልልሶች ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

ተማሪ ሀ፤ የቤት ሥራውን ሰራህ እንዴ?

ተማሪ ለ፤ የቤት ስራዬን ሰርቻለሁ፡፡

ተማሪ ሐ፤ የቤት ስራዬን አልሰራሁም፡፡

ተማሪ ሀ፤ ርዕሰመምህሩ ወደትምህርት ቤት ገባ?

ተማሪ ለ፤ ከጠዋት ገብቶ ነበር፡፡

ተማሪ ሐ፤ ከሰዓት በኋላ ወደቢሮ አልገባም፡፡

ተማሪ ሀ፤ ቁርስህን በልተሀል?

ተማሪ ለ፤ ቁርሴን በልቻለሁ፡፡

ተማሪ ሐ፤ ቁርሴን አልበላሁም፡፡

ተማሪ ሀ፤ ዛሬ አማርኛ ክፍለጊዜ አለን?

ተማሪ ለ፤ አለን፡፡

ተማሪ ሐ፤ ክፍለጊዜ ቢኖረንም መምህሩ ግን አልመጣም፡፡

1. በምልልሱ ውስጥ ተመሳሳይነት ያላቸውን ዓረፍተነገሮችን ለዩ፡፡
2. ተመሳሳይ እንደሆኑ የመደባችሁበትን ምክንያት አስረዱ፡፡
3. ዓረፍተነገሮችን ከአገልግሎታቸው አንጻር አስረዱ፡፡

የክፍል ሥራ

መመሪያ፤ የሚከተሉትን ምልልሶች በማጤን የተጓደሉ ዓረፍተነገሮችን አሟሉ፡፡

ተማሪ ሀ፤  በበቂ መጠን ለፈተና ተዘጋጅተሀል?

ተማሪ ለ፤ ________________________________

ተማሪ ሐ፤ እኔ ግን በበቂ መጠን አልተዘጋጀሁም፡፡

ተማሪ ሀ፤ ________________________________

ተማሪ ለ፤ ምሳዬን በልቻለሁ።

ተማሪ ሐ፤ ምሳዬን አልበላሁም።

ተማሪ ሀ፤ ነገ ወደየት ትሄዳለህ?

ተማሪ ለ፤ ______________________________ (ወደጎንደር ለመሄድ ካቀደ)

ተማሪ ሐ፤______________________________ (የትም የማይሄድ ከሆነ)

ተማሪ ሀ፤ ነገ ትምህርት አለ ወይ?

ተማሪ ለ፤ ______________________________ (መስማማቱን ሲገልጽ)

ተማሪ ሐ፤______________________________(አለመስማማቱን ሲገልጽ)

ተማሪ ሀ፤______________________________

ተማሪ ለ፤ የምኖረው ባሕር ዳር ነው።

ተማሪ ሐ፤ የምኖረው ባሕር ዳር አይደለም።

በተግባሩ የተረዱትን ጭብጥ በተመለከተ የዓረፍተነገር አይነቶችን ከአገልግሎት አንጻር ማብራሪያ በመስጠት ክፍለጊዜው ይቋጫል።

መመሪያ፤ የሚከተሉትን ምልልሶች በመረዳት ከምልልሶች ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

አቤል፤ ያን መጽሐፍ አቀብለኝ።

አቶ ተሾመ፤ ወቸው ጉድ! ጭራሽ የግልብጥ ታዘኝ?

አቶ በላቸው፤ አንተ ስድ አደግ! ወይኔ! አባት ተቀምጦ ልጅ የሚያዝበት ዘመን ላይ እንድረስ!

መምህር፤ የሰጠኋችሁን የቤት ሥራ አውጡ።

ተማሪ ሀ፤ እንዴ! የቤት ሥራ እንደተሰጠን ረሳሁት።

ተማሪ ለ፤ አንተ! ስትቀባጥር መምህሩ እንዳይሰማህ ዝም በል!

1. በምልልሱ ውስጥ ተመሳሳይ አቀራረብና ቅርጽ ያላቸው ዓረፍተነገሮችን ለዩ፡፡
2. ተመሳሳይ እንዲሆኑ የመደባችሁበትን ምክንያት አስረዱ፡፡
3. ዓረፍተነገሮችን ከአገልግሎታቸው አንጻር አስረዱ፡፡

መምህሩ ከተግባሩ በመነሳት ስለዓረፍተነገር አይነቶች ማጠቃለያ ይሰጣሉ፡፡

የዓረፍተ ነገር አይነቶች ከሚይዙት ግስ ብዛት አንጻር

ተግባር

ተማሪዎች የሚከተለውን ምንባብ በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ በምንባቦች ውስጥ ያሉትን ዓረፍተነገረች በጥሞና በማንበብ አንድ ነጠላ ድርጊት ወይም ሁነት የያዙትን ለብቻቸው፣ ከአንድ በላይ ድርጊት ወይም ሁነት ያያዙትን ለብቻቸው (አንድ ግስ የያዙትን በአንድ ወገን ከአንድ በላይ ግስ የያዙትን ደግሞ በሌላ ወገን) መድቡ፡፡ ምደባው ለአሰራር ያመች ዘንድ ከምንባቡ ስር ካሰመራችሁ በኋላ አንድ ግስ ወይም ድርጊትና ሁነት የያዙትን “1”፣ ከአንድ በላይ ግስ የያዙትን ደግሞ “2” ብላችሁ ከዓረፍተነገሮቹ በላይ ጻፉ፡፡

«ባለገንዘብ ለመሆን ስራን አስቀድሞ»

ባለገንዘብ ለመሆን የማይፈልግ ሠው የለም፡፡ ሁሉም ሠው አዱኛ ሠጥ ለጥ ብሎ እንዲገባለት ይመኛል፡፡ ለቤተሰብህ ፍላጐት ማሚያ፣ ለኑሮ ደረጃው ከፍታ ማረጋገጫው ሀይል ገንዘብ ነው፡፡ የእለት እራት የገደዳቸውን እድለቢሶች ለመርዳት የሚያስችለው ሀይል ገንዘብ ነው፡፡

ድህነትን የመጀመሪያ ምርጫው የሚያደርግ ሠው ይገኛል ብለን መገመት ለእርግጠኝነት አያበቃም፡፡ ቢሆንም የዚህ ሠው ምርጫ አክኮ መኖር ከሆነ እርሱ ለማንም የማይጠቅም ፋይዳ የለሽ ነው፡፡ የበታችነት ስሜት የሚሰማው ሀሳበ ስንኩል ነው፡፡

ገንዘብ የፍላጎታችን ማስፈፀሚያና ማሚያ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል እንጂ ስብዕናችን አይለውጠውም፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ሠዎች ስለገንዘብ የሚኖራቸው አመለካከት

እንቆቅልሽ ነው፡፡ ያለቅጥ ያመልኩበታል፡፡ ውዳሴ መዝሙራቸው «ገንዘብ ወይንም ሞት» የሚል ነው፡፡ ከምንም አስበልጠው ለገንዘብ ነው ቅድሚያ የሚሠጡት፡፡

ሆኖም ግን እነዚህ ሠዎች ገንዘብን ይውደዱት እንጅ እንደስግብግብነታቸው የተረፋቸው አይደሉም፡፡ እንዲያውም የሚያወላዳ ገንዘብ አይኖራቸውም፡፡ «ለምን መሠለህ?» ከሁሉም በፊት ምኞታቸው ገንዘብ ማግኘት ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ነው፡፡ ገንዘብ ከሜዳ የሚታፈስ ይመስላቸዋል፡፡ ባለ ገንዘብ ለመሆን የሚያበቃቸውን ዘር ሳይበትኑ ምርት ለማፈስ መሞከር ከንቱ መቃተትን ይረሳሉ፡፡

ለገንዘብ ዘሩ ስራ ነው፡፡ አገልግሎትን አስቀድም፡፡ ለዚህ ነው ከሁሉም በፊት ስራና አገልግሎት አስቀድም የሚባለው፡፡ አንተም ስራ አስቀድሞ ከዚያ በኋላ ገንዘብ የስራ ውጤትህን ፈር ተከትሎ ይመጣል፡፡

ለሠዎች አገልግሎት አበርክት፡፡ ስራ ወዳድ ሁን፡፡ ምንጊዜም ቢሆን ሠዎች ከሚጠብቁህ በላይ ሆኖ ለመገኘት ተጣጣር፡፡ አዲስ ገንቢ ሀሳብ ማመንጨትና በየጊዜው ችሎታን ማዳበርም በጋ ከክረምት የማይወይብ የገንዘብ ዘር ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ የገንዘብ ዘር የሚያፈራው ገንዘብ ነው፡፡ ቀና የስራ ባህልህን ዝራና አሳድግ ከዛ የገንዘብ ምርት እያፈስክ በኮሮጆህ ጠቅጥቅ «ሁሉ በጄ ሁሉ በደጄ» ይሉሀል ይህ ነው፡፡ አንተ ማርክ ሰብሳቢ ስለሆነክ ወደጥያቄው ተሻገር፡፡ መልካም ውጤት፡፡

ተማሪዎች በተባላችሁት መልኩ በመመደብ አስቀመጣችሁ? መልካም!! አሁን ደግሞ የመለሳችሁትን መልስ ጥንድ ጥንድ በመሆን ስለትክክለኛነቱ ተወያዩበት፡፡

በተባላችሁት መልኩ ተግባሩን ስለሰራችሁት ኮርቸባችኋለሁ፡፡ ዐረፍተነገሮችን ከመዋቅር (በውስጣቸው በሚያዙት የተዋቃሪ ዓይነት) አንጻር ነጠላ፣ ድርብ፣ ድብልቅና ድርብ ድብልቅ ዐረፍተነገሮች ብሎ መክፈል ይቻላል፡፡

ነጠላ ዐረፍተነገር የሚባለው በውስጡ አንድ ግስ ብቻ የያዘ ዐረፍተነገር ነው፡፡ ነጠላ ዐረፍተነገር ተራ ዐረፍተነገር ወይም መደበኛ ሐረግ በመባልም ይታወቃል፡፡ የሚዋቀረውም ከተራ ስማዊ ሐረግና ከተራ ግሳዊ ሐረግ ወይም ከአንድ ባለቤት እና ከአንድ ማሰሪያ አንቀጽ (ግስ) ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ናትናኤል ደብተር ገዛ፡፡

ለ. ራህመት ለወንድሟ ደብዳቤ ጻፈች።

እነዚህ ዐረፍተነገሮች ገዛ፣ ጻፈች የሚሉ አንድ አንድ ግሶችን ብቻ የያዙ ነጠላ ዐረፍተነገሮች ሲሆኑ፣ በስማዊ ሀረጋቸው ክፍልም ሆነ በግሳዊ ሀረጋቸው ክፍል ምንም ዓይነት ተጨማሪ ግስ የላቸውም።

ድርብ ዐረፍተነገር ኹለት ነጠላ ወይም ተራ ዐረፍተነገሮችን በወደረኛ መስተፃምር በማያያዝ የሚዋቀር የዐረፍተነገር ዓይነት ነው። ወደረኛ መስተፃምሮቹም አያያዥ ተብለው ይጠራሉ። በአያያዥነት ከሚታወቁት መካከል ግን፣ ና፣ ነገር ግን፣ ይሁን እንጂ፣ እንጂ፣ ቢሆንም ግን የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ምሳሌ፣ ሀ. በደንብ ተምራችኋል፤ ይሁን እንጂ ፈተናውን አልሰራችሁትም። ለ. ተማሪው ምሳውን በላና ወደትምህርት ቤት ሄደ።

ድብልቅ ዐረፍተነገር ከአንድ መደበኛ ወይም ነፃ ዐረፍተነገርና ከአንድ ወይም

ከአንድ በላይ በሆኑ ጥገኛ ዐረፍተነገሮች የሚዋቀር ነው። ምሳሌ፣ ሀ. አማረ ኤልሳቤጥ ቤት እንደሰራች ያውቃል። ለ. ኢክራም ባለቤቷ ስለመጣ ተደሰተች።

የተሰመረባቸው ጥገኛ ዐረፍተነገሮች ሲሆኑ፣ እንደቅደምተከተላቸው በመደበኛ

ዐረፍተነገሮቹ ውስጥ የገቡ (ሀ) መሙያ እና (ለ) አጎላማሽ ናቸው።

ድርብ ድብልቅ ዐረፍተነገር ቢያንስ ከኹለት የሚያስሩ ግሶችና አንድ ጥገኛ ሐረግ ወይም ዐረፍተነገር ይዋቀራል። የዓረፍተነገሩ መዋቅር ኹለት መደበኛ ሐረጋትና አንድ ጥገኛ ሐረግ ይኖረዋል። ከአንድ በላይ ጥገኛ ሐረጋትና ከኹለት በላይ መደበኛ ሐረጋትም ሊኖሩት ይችላል።

ምሳሌ፣ ሀ. ዝናብ ስለዘነበ ጃንጥላዋን ዘረጋችና ወደቤቷ ሄደች።

ስለዘነበ - ጥገኛ ሐረግ

ዘረጋች እና ሄደች - የሚያስሩ ግሶች ናቸው።

ለ. ደመናው ከብዷል፤ ሰማዩም ጠቁሯል፤ ብልጭታውም በዝቷል፤ ስለዚህ ጥቂት ቆይቶ መዝነቡ ስለማይቀር በጊዜ ወደቤት እንሂድ።

ቆይቶ እና ስለማይቀር - ጥገኛ ሐረጋት

ከብዷል፣ ጠቁሯል፣ በዝቷል እና እንሂድ የሚያስሩ ግሶች ናቸው።

(ጌታሁን፣ 2013 ለማስተማሪያነት እንዲያመች ተደርጎ የቀረበ)

## ጊዜ

ይዘቱ የሚቀርበው፦ በምንባብ፣ በዓረፍነገር፣ በትግበራ

መመሪያ፤ የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች በጥሞና አንብቡና ከዓረፍተነገሮች ቀጥለው የቀረቡ ተግባራት አከናውኑ።

1. የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት የስራ አመራሮች ቀጣይ ሳምንት ስብሰባ ያደርጋሉ።
2. ባለፈው ክረምት በአብዛኛው የሃገራችን ክፍል ከፍተኛ ዝናብ ዘንቦ ነበር።
3. በቀጣዩ ቀን በብሔራዊ ቲያትር የስነ-ጽሁፍ ውድድር ይካሄዳል።
4. ዛሬ መምህሩ ለተማሪዎቹ የፈተና ወረቀት እየመለሰ ነው።
5. እስክንድር ባለፈው ሳምንት ግብሩን ከፍሏል።
6. ሀኪሙ ታማሚውን እየመረመረ ነው።
7. ትናንት በሠራው መጥፎ ሥራ እጅግ አዘነ።
8. እነሱ ነገ ወደሀገራቸው ይሄዳሉ።
9. አስቴር ትናንት እዚያ ነበረች።
10. ነብያት አሁን መጽሐፍ ታነባለች።
11. ሙስጠፋ ከነገወዲያ የትምህርት መሣሪያዎችን ይገዛል።
12. ያዕቆብ ትናንት ብዙ በራሪ ወረቀቶችን አነበበ።
13. ንብረት ኹለት ህንጻ ገነባች።
14. ሌባው ተቀጥቶ ነበር፤ ግን ዛሬም ሊማር አልቻለም።
15. ሰውየው አሁን መጥቷል።
16. ሰዓዳ ቤት ገዛች።
17. ልጆቹ እየተጫወቱ ነው።
18. ተማሪዎቹ እያነበቡ ነው።
19. ሙሉ ቡና እያፈላች ነው።

20.ዐለሙ <u>ነገ</u> ከወልድያ ወደባሕር ዳር <u>ይሄዳል</u>፡፡

21.ጀማል መኪና <u>ገዝቷል</u>፡፡

22.ማርያም ወርቅ ዶሮ <u>ገዝታ ነበር</u>፡፡

23.ወይንሸት <u>ትናንት</u> መጽሐፍ <u>ገዛች</u>፡፡

ተግባር

ሀ. በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ውስጥ ተመሳሳይ አቀራረብና ቅርጽ ያላቸው ዓረፍተነገሮችን ለዩ፡፡

ለ. ተመሳሳይ እንዲሆኑ የመደባችሁበትን ምክንያት አስረዱ፡፡

ሐ. በዓረፍተነገሮች የተገለጹት ድርጊቶቹ ወይም ሁነቶች የተከናወኑበትን ወይም የሆኑበትን ጊዜ ግለጹ፡፡

መምህሩ ከሰሯቸው ተግባራት በመነሳት የጊዜ አይነቶችን በየምድባቸው ያስረዳሉ፡፡ ትምህርቱን ለማጠናከር የሚከተሉትን ተግባራት እንዲተገብሩ ያደርጋሉ፡፡

ሀ. የትላንት ዕለት ውሏቸውን እንዲጽፉ ያዛሉ፡፡

ለ. በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተማሪዎችና በመምህሯ የሚከናወኑ ተግባራትን እየተመለከቱ እንዲጽፉ ያዛሉ፡፡

ሐ. ነገ ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት እንዲጽፉ ያደርጋሉ፡፡

በተጠቀሱት ተግባራት ዐውድነት የጻፏቸውን ጽሑፎች መሰረት በማድረግ የጊዜ አይነቶች በምድብ በምድባቸው እንዲመደቡ ተደርገው ክለሳ ይደረግላቸዋል፡፡

ተግባር

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በጥሞና በማንበብ የተፈጸመ (የተጠናቀቀ) ድርጊት ያለባቸውን ዓረፍተነገሮች በእርሳስ፣ እየተፈጸመ ያለ ጊዜ ያለባቸውን ዓረፍተነገሮች በቀይ እስክብሪቶ እንዲሁም ገና ለወደፊት የሚፈጸሙትን ደግሞ በሰማያዊ እስክብሪቶ አስምሩባቸው (ምንባቡ በቡድን በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ተባዝቶ ይሰጣቸዋል)፡፡

# የዓለም መጨረሻ

“የመጨረሻውን 48 ሰዓታት እንዴት ማሳለፍ ትፈልጋለህ?” የሚል ፅሁፍ ማንበብ ጀመርኩና ሰለቸኝ፡፡ በዛ ላይ ፅሁፉ ረጅም ነው፡፡ በምድር ላይ ከቀረችኝ ሁለት ቀን ላይ የማይረባ ጽሁፍ በማንበብ ሽራፊ ሰከንድ ማሳለፍ አልፈለግሁም፡፡ ጋዜጣውን አጠፍኩት፡፡ የተቀመጥኩበት ካፌ በሰው ተሞልቷል፡፡ ሁሉም በአንድ ላይ እያወራ ነው፡፡ በአንድ ላይ እያወራ፣ በአንድ ላይ ይደማመጣል፡፡ ካፌው ሻይና ማኪያቶ ማቅረብ ካቆመ ቀናት አልፎታል፡፡ ሰርግ ነው የሚመስለው፡፡ ውስኪ በየጠረጴዛው ተቀምጧል፡፡ ከቀኑ አራት ሰዓት ይላል ሰአቴ፡፡ ድካም ይሰማኛል ግን መተኛት አልቻልኩም፡፡ ማንም መተኛት አይሻም፡፡

አንድ ወር ቀደም ብሎ ገና ዜናው ሲሰማ፣ የሰው ባህሪ ተቀየረ፡፡ “ከዚህ በፊትም እንደዚህ ተብሎ ነበር” ብሎ ዜናውን አላምንም ያለ፣ በማህበራዊ ሚዲያ ሲፃፍ ከረመ፡፡ “አላምንም” የሚለው ሁሉ ግን የምድርን መጥፋት ፈላጊ ነበር፡፡ ቀስ እያለ ሁሉም ዜናውን እየተቀባበለው ነው፡፡ ባለሀብቱ ያከማቸውን ሀብት እያወጣ ለደሀ ለመስጠት ልምምጥ ጀመረ፡፡ ግን ደሀውም ዜናውን ሰምቷልና አይፈልግም፡፡ “ሞኝህን ፈልግ፤ በአንተ የግፍ ገንዘብ ማን ኩነኔ ይገባል” ብሎ ሀብታም ላይ ተሳለቀ፡፡

አንድ ሳምንት ሲቀር የመንግስት አገልግሎት ሁሉ ነፃ ሆነ፡፡ ትራንስፖርት ነፃ፣ መብራትና ውሃ ነፃ…፡፡ ባንክ ቤቶች፤ ”በነፃ ብር ካላበደራችሁ ትቃጠላላችሁ” የሚል የወመኔ ቡድን ስላሰጋቸው፣ ብራቸውን ጠቅልለው፣ በራቸውን ዘግተው ተሰወሩ፡፡ በየካፌው ነፃ መጠጥ እንዲቀርብ ተደነገገ፡፡ ሰው ሁሉ ሰካራም ሆነ፡፡ ግን ምንም አይነት አምባጓሮ አይታይም፡፡ በሆነው ነገር “ደስተኛ እየሆነ ይመጣል” የሚል አመለካከት መስፋፋት ጀመረ፡፡

በበረሀና በህገ ወጥ መንገድ የተሰደዱ፣ በህጋዊ መጓጓዣ ሀገራቸው መግባት ያዙ፡፡ “ለካ ተስፋ ነበር ሰውን ያባለገው” የሚል አስተያየት መናፈስ ጀመረ፡፡ ለካ ለመኖር የሚያደርገው መፍጨርጨር ነው የሰውን ልጅ ክፉ አድርጎት የነበረው፡፡ እና እኔም ዘና ብያለሁኝ፡፡ ማግኘት የምፈልጋቸው ሰዎች የሉም፡፡ ቢኖሩም የምናመራው ወደ አንድ መጨረሻ ስለሆነ እዛው እንገናኛለን፡፡ መለያየት አለመኖሩ ሁሉንም አረጋግቶታል፡፡ ዓለም ላይ በተለያየ ስፍራ እየተካሄደ ስላለው ወቅታዊ ሁኔታ ይዘገባል፡፡ ዘገባው

ለመጀመሪያ ጊዜ ፖለቲካም ሆነ ውሸት የሌለበት ሆነ፡፡ ዘገባውን የሚከታተሉ ይከታተሉታል፡፡ ግን ብዙም ትኩረት አይሰጡትም፡፡

የክፉ ጊዜ አትራፊ ነጋዴዎችም አትርፈው የሚሸሸጉበት እንደሌለ ማወቃቸው አልቀረም፡፡ የሰበሰቡትን መስጠት ላይ አተኮሩ፡፡ ግን የሚሰጡት ነገር እንደ ቀድሞው ፈላጊ አልነበረውም፡፡ ዋጋው ያልረከሰ ሙዚቃ ብቻ ነው፡፡ ሁሉም እስከሚሞት መስማት የሚፈልገው ሙዚቃ አለው፡፡ በጋራ ወይም በጆሮው ላይ ማዳመጫ ሰክቶ ያዳምጣል፡፡ የመጨረሻው የማስፈራሪያ ደወል ቢደወልም የፈራ ግን አልነበረም፡፡ በሚገርም ሁኔታ ሁሉም "የሰው ልጅ መጥፊያው መቃረቡ ጥሩ ነው" ብሎ ያምናል፡፡ "መጥፋት የለበትም … እናድነው" የሚሉ ሳይንሳዊ ክርክሮች ከስመዋል፡፡

በሙዚቃው ውስጥ ተውጠዋል፡፡ "የቧንቧ ውሀ መጠጣት ጤናዬን ያሰጋዋል"… ብለው የተዉት ያገኙትን ውሃ መጠጣት ጀምረዋል፡፡ በጥንቃቄ የታሸገና ብዙ ብር ይገዙት የነበረውን ውሃ፣ አትክልታቸውን እያጠጡበት ይሳሳቃሉ፡፡ አትክልቶቹ የተመረጠ ውሃ በመጠጣታቸው እንደሚደሰቱ ያውቃሉ፡፡ ከራሳቸው ፍርሐት ነፃ መውጣታቸውን ለመግለፅ ይመስላል ይሳሳቃሉ፡፡ ፀሎት ማድረስ የሚፈልግም በጎዳና ተንበርክኮ ይጮሀል፡፡ እንደ ቀድሞው ለማስመሰል ወይ ለታይታ እንዳልሆነ ግልፅ ነበር፡፡ በሚገርም ሁኔታ ብዙ የአዕምሮ ቀውስ ያለባቸው ሰዎች ድንገት ጤነኛ ሆኑ፡፡ ለዘመናት የሆስፒታል አልጋ የተቆጣጠሩ፣ የምድር ፍፃሜ ዜና እየቀረበ ሲመጣ፣ ከህመማቸው እያገገሙ ተነሱ፡፡

ለካ ሰብዕና ይህንን ያህል ያረጀ ልብስ ሆኗል? ብዬ አስባለሁ፡፡ እንቅልፍ ባልተኛም … መጠጥ ባበዛም፣ ንዴትና ጭንቀት ሳይሆን ሰላም ነው የሚሰማኝ፡፡ በቃ ሰው ያረጀውን ህልውናውን መገላገል ፈልጓል፡፡ እጣ ፈንታ ሊገላግለው በመምጣቱም ደስተኛ ሆኗል፡፡ ደግሞ ይኼንን ደስታውን የሚነጥቀው ማንም የለም፡፡ ማንም ቀድሞ ወይንም ዘግይቶ አለመሞቱ፤ አንድ ላይ በአንድ ቅፅበት፣ ከጠፈር በሚመጣ አለት መጨፍለቁ እኩል አድርጎታል፡፡

እኩልነት ለካ በዚህ መልክ ብቻ ነው እውን ሊሆን የሚችለው እያልኩ አስባለሁ፡፡ ግን በጣም ለጥጬ አላስብም፡፡ ያሰብኩትንም ለሰው አላካፍልም፡፡ ጭንቀት ውስጥ አይደለሁኝም፡፡ ሀሳቤን በማካፈል የምገላገለው ነገር ስለሌለ፣ ለምን የሌላውን ጥሞና

አጨናንቃለሁ? የመጨረሻዎቹ አስራ ሁለት ሰዓታት ሲደርሱ፣ ምድር በሀይማኖት መጻህፍት ድሮ ነበረች እንደተባለችው ሆነች፡፡ ሁሉም ሰው የዋህና እውነተኛ፣ ተንኮልም ሆነ የመብለጥ ፍላጎት የሌለው ሆነ፡፡ ንግግሩን ቀነሰ፡፡ መጠጥ ሳይጠጣ መስከር ቻለበት፡፡ ስካሩ አዎንታዊ የሚባለው ነው፡፡ የሚያንገዳግድ ወይንም የሚያሰዳድብ ወይንም አምባጓሮ ቀስቅሶ የሚያጋጭ ሳይሆን የመሬት ስበትን ቀንሶ፣ በአየር ላይ የሚያንሳፍፍ አይነቱ ነበር፡፡

ሁሉም ሰው አዳም ፍሬውን ከመብላቱ በፊት የነበረው ልበ ሙሉነት በገፅታው ላይ ይታያል፡፡ ሁሉም ሰው ከፍርሐት ነፃ ሆኗል፡፡ ሁሉም ሰው የሰራውን ሀጢዓት ረስቷል፡፡ አዲስ ሰብዕናው ድሮ ሀጢአት ለመስራት ከተገደደው ሰብእናው ጋር ተሰነባብቷል፡፡ ከመሰነባበትም በላይ የቀድሞ ሰብዕናውን ከመወለድ በፊት ወይም ከሞት በኋላ እንዳለ ቅዠት ፈፅሞ ረስቶታል፡፡

የመጨረሻዎቹ አስራ ሁለት ሰዓታት እየተቀነሱ ሲመጡ የሰዓት ፅንሰ ሀሳብ ራሱ ትርጉም አልባ ሆኖ ነበር፡፡ በስምምነት ወይንም በድንጋጌ ሳይሆን በቃ ሰዓት ራሱ ሰዓት አልፎበታል፡፡ እንዳለፈበት ደግሞ ከራሱ ከሰዓቱ በስተቀር የሚገደው አላገኝም፡፡ የመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ሲደርሱ በሰዓት አማካኝነት ሳይሆን ህያው ቀልቡ በየነብሱ ውስጥ ምልክት የሰጠው ሁሉ ወደ አደባባይ ወጣ፡፡ እንደ አመፅም እንደ ትዕይንተ ህዝብም ያልሆነ መሰባሰብ ተፈጠረ፡፡

እኔም ራሴን እንደ ግለሰብ ከዘነጋሁት ብዙ ሰዓታት እንዳለፉ እንኳን አላውቅም፡፡ ሁሉም ሀገር በስልጣኔ ወይንም ምጣኔ ሀብት ሳይሆን በሰውነቱ እኩል ሆኗል፡፡ መሆኑን እንኳን ማወቅ ግን አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ሰው ተፈጠረ፡፡ በዛ …፡፡ እናም ጠፋ፤ አለቀ፡፡ ሲያልቅ ሁሉም ወደ ሰማይ አንጋጧል፡፡ እየመጣ ያለው ነገር ብርሃኑ ፊትን ያቀልጣል፡፡ ግን ማንም ከብርሃኑ ለመሸሽ ያኀበሰ ወይንም ያኀበደደ አልነበረም፡፡

ተማሪዎች የተሰጣችሁን ተግባር በመመሪው መሰረት ተገበራችሁ? በጣም ጎበዞች!! አሁን በቡድናችሁ አማካይነት በእርሳስ ያሰማራችሁባቸውን፣ በቀይ እንዲሁም በሰማያዊ እስክብሪቶ ያሰመራችሁባቸውን እስክብሪቶዎች ያሰመራችሁባቸውን ደግማችሁ በማየት፤

1. የሚያመሳስላቸውን ባህርይ አስረዱ፡፡

2. ያልተፈጸመ፣ ገና የሚፈጸምና እየተፈጸመ ያለ መሆኑን በምን እንደለያችሁ አብራሩ፡፡

3. ተፈጽመው ያለፉ ናቸው ብላችሁ የለያችኋቸውን ዓረፍተ ነገሮች በቅርብ ያለፉ፣ ካለፉ ብዙ ጊዜ የሆናቸውና የተፈጸሙበት በግልጽ የማይታወቁትን ለዩ፡፡

መምህሩ ለተግባራቱ በቂ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

ተግባር

ተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳው ላይ የሚጻፉላችሁን ዓረፍተነገሮች በጥሞና ተመልከቷቸው፡፡ ዓረፍተነገሮቹ፡-

1. የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት የስራ አመራሮች ቀጣይ ሳምንት ስብሰባ ያደርጋሉ፡፡
2. ባለፈው ክረምት በአብዛኛው የሃገራችን ክፍል ከፍተኛ ዝናብ ነበር፡፡
3. በቀጣዩ ቀን በብሔራዊ ቲያትር የስነ-ጽሁፍ ውድድር ይካሄዳል፡፡
4. ዛሬ መምህሩ ለተማሪዎቹ የፈተና ወረቀት እየመለሰ ነው፡፡
5. እስክንድር ባለፈው ሳምንት ግብሩን ከፍሏል፡፡
6. ሀኪሙ ታማሚውን እየመረመረ ነው፡፡
7. ትናንት በሠራው መጥፎ ሥራ እጅግ አዘነ፡፡
8. እነሱ ነገ ወደሀገራቸው ይሄዳሉ፡፡
9. አስቴር ትናንት እዚያ ነበረች፡፡
10. ነብያት አሁን መጽሐፍ ታነባለች፡፡
11. ሙስጠፋ ከነገወዲያ የትምህርት መሣሪያዎችን ይገዛል፡፡

12.ያዕቆብ ትናንት ብዙ በራሪ ወረቀቶችን አነበበ።

ተማሪዎች የተዘረዘሩት ዓረፍተነገሮች የትኛውን ጊዜ የሚያሳዩ ይመስሏችኋል። መልካም!!! ጊዜዎችን የአሁን፣ የትንቢትና የሐላፊ ጊዜ ብላችሁ እንድትመድቡ ያደረጓችሁ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

እንደገለጻችሁት ከዓረፍተነገሮቹ ጋር አብረው የሚመጡ የጊዜ ገላጭ ቃላት የዓረፍተነገሮችን ጊዜ ለመመደብ ያግዛሉ። የመጀመሪያውን ዓረፍተነገር እንደምትመለከቱት ቀጣይ ሳምንት የሚል የጊዜ ገላጭ በመኖሩ ምክንያት የትንቢት ጊዜ ለማለት ችላችኋል። በጥያቄ ቁጥር አራት ዛሬ የሚለውን የጊዜ ገላጭ በመመልከት የአሁን ጊዜ እንደሆነ ጠቁማችኋል። በጥያቄ ቁጥር አምስት ደግሞ ባለፈው ሳምንት የሚል የጊዜ ገላጭ በመኖሩ ምክንያት የሐላፊ ጊዜ በማለት መልሳችኋል። ይህም በዓረፍተነገሮች ውስጥ አብረው የሚካተቱ የጊዜ ገላጮች ጊዜን ለመለየት እንደሚያግዙ ነው።

ሆኖም ግን ሁልጊዜም ቢሆን ጊዜን ለመለየት የጊዜ ገላጮችን ብቻ ተመልክቶ መወሰን ስሕተት እንድንሰራ ሊያደርግ ይችላል። ለዚህም አስረጂ እንዲሆን ዘጠነኛውን ዓረፍተነገር ተመልከቱ። የጊዜ ገላጩ "አሁን" ቢሆንም ግሱ ላይ የትንቢት አመልካች ቅጥያ በመኖሩ ምክንያት የትንቢት ጊዜ ሊሆን ችሏል። "አሁን መጣ" ቢልም በተመሳሳይ ግሱ ላይ በተቀጠለው የየዋህ ሐላፊ ቅጥያ አመልካች ምክንያት የሐላፊ ጊዜ ሆኗል። ስለሆነም በግሱ ላይ የሚጨመሩ ቅጥያዎችና የግሱ ባህርይ ጊዜን ለመለየት ያግዛሉ።

ግሶች ድርጊት ወይም ሁነት እንደተፈጸመበት ወይም እንደሚፈጸምበት ጊዜ ቅርጻቸውን ይለዋውጣሉ። ጊዜ የምንለው ድርጊቱ ወይም ሁነቱ የተፈጸመበት ወይም የሚፈጸምበትን ወቅት ነው። ይህም ድርጊቱ ከሚነገርበት ጊዜ አንጻር ሲታይ ነው። ከንግግሩ ወቅት ቀድሞ ያለው ጊዜ የኣላፊ ጊዜ፣ በንግግሩ ወቅት ከሆነ የአሁን ጊዜ እና ገና ያልተፈጸመ ከሆነ የትንቢት ጊዜ ተብሎ ይገለጻል።

የኣላፊ ጊዜ፣ አንድ ድርጊት ባለፈ ጊዜ የተከናወነና የተፈጸመ ከሆነ፣ ጊዜው

አላፊ፣ ግሱ ደግሞ የአላፊ ጊዜ ግስ ይባላል፡፡ የአላፊ ጊዜ የዋህ አላፊ፣ የቅርብ አላፊ እና የሩቅ አላፊ ተብሎ በሦስት ይከፈላል፡፡ ድርጊቱ ሲፈጸም ንግግሩ ለተፈጸመበት ጊዜ የሚርቅ ሲሆን የሩቅ አላፊ፣ የሚቀርብ ሲሆን ደግሞ የቅርብ አላፊ ይባላል፡፡ ድርጊቱ የተፈጸመበት ጊዜ ርቀት ተለይቶ የማይታወቅ ከሆነ ደግሞ ጊዜው የዋህ አላፊ ይሆናል፡፡

ምሳሌ፣ (ሀ). ንብረት ሁለት ህንጻ ገነባች፡፡ (የአላፊ ጊዜ)

(ለ). ሌባው ተቀጥቶ ነበር፤ ግን ዛሬም ሊማር አልቻለም፡፡ (የሩቅ አላፊ)

(ሐ). ሰውየው አሁን መጥቷል፡፡ (የቅርብ አላፊ)

(መ). ሰዓዳ ቤት ገዛች፡፡ (የዋህ አላፊ)

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች (ሀ) ድርጊቱ ቀድሞ የተፈጸመ በመሆኑ ግሱ (ገነባች) የአላፊ ጊዜን ይገልጻል፡፡ (ለ) ድርጊቱ ነበር በሚል ረዳት ግስ የተገለጸ በመሆኑ ከሌላ ድርጊት ቀድሞ መፈጸሙን ይነግረናል፡፡ የግስ ጊዜውም የሩቅ አላፊ ነው፡፡ የሩቅ አላፊ ነበር ከሚለው ረዳት ግስ በተጨማሪ በቦዝ አንቀጽ ቅርጽ (በልቶ፣ ጠጥቶ፣ ሰርቶ ወዘተ.) ሊገለጽ ይችላል፡፡ (ሐ) ድርጊቱ ከቅርብ ጊዜ በፊት የተፈጸመ (መጥት-ኦ-ኣል) መሆኑን ስለሚያሳይ የቅርብ አላፊ ነው፡፡ የቅርብ አላፊ የሚገለጸው በቦዝ አንቀጽ ቅርጽና በረዳት ግስ /-ኣል/ ነው፡፡ (መ) ድርጊቱ የተጠናቀቀበትን ጊዜ ለይቶ ስለማያሳይ የዋህ አላፊ ነው፡፡ ሆኖም ግን በዚህ መልኩ የሚዋቀሩ ዐረፍተነገሮች ድርጊቱ ይፈጸም እንጂ፣ የተፈጸመበትን ጊዜ አይጠቁሙም፡፡ ይህን ችግር ለማስወገድ ጊዜ አመልካች ግስ ገላጮች ከግሶቹ ጋር መዋቀር ይችላሉ፡፡ በዚህም መሠረት (መ) ‹‹ትናንት›› የሚል ጊዜ አመልካች የግስ ገላጭ ቢጨመርበት ‹‹ሰዓዳ ትናንት ቤት ገዛች›› በሚል መግለጽ ይቻላል፡፡

የዋህ ሐላፊን ለመለየት ከማሰሪያ አንቀጹ ላይ የሚከተሉት ቅጥያዎች ተቀጥለው እናገኛለን፡፡

| | ቅጥያ | ምሳሌ |
|---|---|---|
| እኔ፡- | -ኩ/-ሁ | = ሄድኩ/መጣሁ |
| እኛ፡- | -ን | = ሄድን/መጣን |

አንተ፡-　-ክ/-ህ　= ሄድክ/መጣህ

አንቺ፡-　-ሽ　= ሄድሽ/መጣሽ

እናንተ፡-　-ኣችሁ　= ሄዳችሁ/መጣችሁ

እሱ፡-　-ኧ/-ኣ　= ሄደ/መጣ

እሷ፡-　-ኧች/-ኣች = ሄደች/መጣች

እነሱ፡-　-ኡ　= ሄዱ/መጡ

የአሁን ጊዜ፣ አንድ ድርጊት ወይም ሁነት በመፈጸም ላይ ያለ ወይም አሁን እየተፈጸመ መሆኑን የሚያመለክት ጊዜ ነው፡፡

ምሳሌ፣ (ሀ). ልጆቹ እየተጫወቱ (እየ-ተጫወቱ) ነው፡፡

(ለ). ተማሪዎቹ እያነበቡ (እየ-አነበቡ) ነው፡፡

በእነዚህ ምሳሌዎች /እየ-/ በግሶቹ ላይ ቅድመአምድ ሆኖ በመቀጠል ድርጊቶቹ እየተከናወኑ ያሉና ያልተጠናቀቁ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ መጨረሻ ላይ ያለው /ነው/ ደግሞ ረዳት ግስ ሆኖ በመግባት ጊዜው የአሁን መሆኑን ይጠቁማል፡፡

የትንቢት ጊዜ፣ አንድ ድርጊት ወይም ሁነት ወደፊት የሚፈጸም መሆኑን የሚጠቁም ጊዜ ነው፡፡ ይህ ጊዜ በካልኣይ አንቀጽ (ያልተጠናቀቀ ድርጊት መሆኑን የሚያሳይ) ግስ እና በረዳት ግስ /-ኣል/ ቅንጅት ይገለጻል፡፡

ምሳሌ፣ (ሀ). ልጁ ነገ ትምህርት ቤት ይሄዳል፡፡ (ለ). ልጁ ልቦለድ መጽሐፍ ያነባል፡፡

የመጀመሪያው ምሳሌ (ሀ) በማያሻማ ሁኔታ፣ ‹‹ነገ›› በሚል ጊዜ አመልካች ወደፊት የሚፈጸም ድርጊት መገለጹን እናያለን፡፡ በሁለተኛው (ለ) ዓይነት የሚዋቀሩ ዐረፍተነገሮች ግን፣ የአሁን ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ ወይም አዘውትሮ የሚያነብ መሆኑን ሊጠቁሙ ስለሚችሉ ጊዜያቸው የሚያሻማ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ መዋቅሩ አሻሚ እንዳይሆን ጊዜ አመልካች ተዋቃሪ ይገባበታል፡፡ ዐረፍተነገሩም፣ ‹‹ነገ›› የሚል ጊዜ አመልካች ተዋቃሪ ቢጨመርበት ‹‹ልጁ ነገ ልቦለድ መጽሐፍ ያነባል›› የሚል መሆንን ይችላል፡፡

የትንቢት ጊዜን ለመለየት በማሰሪያ አንቀጹ ላይ የሚቀጠሉ ቅጥያዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

እኔ፡- -እ.....ኣል- = እመጣለሁ

እኛ፡- እን.....ኣል- = እንመጣለን

አንተ/አንቺ/እናንተ/እሷ፡- ት.....ኣል- = ትመጣለህ/ትመጫለሽ/ትመጣላችሁ/ትመጣለች

እሱ/እነሱ፡- ይ.....ኣል- = ይመጣል/ይመጣሉ

፩. የሚከተሉት ዐረፍተነገሮች የተገለጹበትን የግስ ጊዜያት ለይታችሁ ካወጣችሁ በኋላ ጊዜውን ለመለየት የተጠቀማችሁባቸውን ብልሀቶች ጠቁሙ፡፡

1. ሙሉ ቡና እያፈላች ነው፡፡
2. ዐለሙ ነገ ከወልድያ ወደባሕር ዳር ይሄዳል፡፡
3. ጀማል መኪና ገዝቷል፡፡
4. ማርያም ወርቅ ዶሮ ገዝታ ነበር፡፡
5. ወይንሸት ትናንት መጽሐፍ ገዛች፡፡

፪. በሚከተሉት የግስ ጊዜያት ሁለት ሁለት ዐረፍተነገሮች ጽፋችሁ አሳዩ፡፡ ዓረፍተነገሮችን ካዋቀራችሁ በኋላ ጊዜዎችን ለመፈረጅ የተጠቀማችሁበትን ብልሀት አመልክቱ፡፡

ሀ. የዋህ ሐላፊ ለ. የቅርብ ሐላፊ ጊዜ

ሐ. የትንቢት ጊዜ መ የአሁን ጊዜ

ተማሪዎች ተግባራትን በታዘዛችሁት መልኩ በመስራታችሁ አኩርታችሁኛል፤ እንናንተም ልትኮሩ ይገባል፡፡

## የቃል ክፍሎችና የሐረግ አይነቶች

ይዘቶች የሚቀርቡት፡- በምንባብ፣ በዓረፍተነገር

ተግባር

ተማሪዎች ቀጣዩን ምንባብ በጥሞና አንብቡና ከእያንዳንዱ የቃል ክፍሎች አስር፣ አስር ቃላት እንዲሁም ከእያንዳንዱ የሀረግ አይነቶች አምስት አምስት ሀረጎችን በመምረጥ አውጡ፡፡

ምንባብ

በጣም አሳዛኝ ታሪክ ስለሆነ ልብ ብለው ያንብቡት» ታሪኩ እውነተኛ ይሁን እንጂ የፊልም ባለሞያዎች ወደ ፊልም ቀይረው እንባ በሚያራጭ መልኩ ሰርተውታል፡፡ እኔም የታሪኩ ጭብጥ ስለ መሰጠኝና እናንተም እንደምትወዱት ስላመንኩ ታሪኩን አጠር አጠር አርጌ አንዳንድ የራሴንም ሀሳብ አክዬበት ላካፍላችሁ ወደድኩ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ በሊባኖስ ሀገር ከሚገኘው በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ መምህሯ ክፍል ገብታ ስታስተምር ከተማሪዎቹ አንዱ ይነሳና "መምህር እቃ ተሰርቂያለሁ" ይላል፡፡ መምህሯም በስርቆቱ እጅግ ተበሳጭታ የተሰረቀው እቃ ምን እንደሆነ ካጣራች በኋላ ተማሪዎች ለፍተሻ እንዲዘጋጁ አደረገችና ፍተሻዋን ቀጠለች፡፡

በፍተሻው ሰዓት ታዲያ አንዲት እድሜዋ 10 ኣመት የማይሞላ ተማሪ ተራዋ ደርሶ ቦርሳዋን እንድትከፍት ስትጠየቅ አሻፈረኝ ትላለች፡፡ መምህሯም በንዴት ጡፋ ምራቋን ፊቷ ላይ ተፍታባት አንቺ ሌባ ኣንቺ ነሽ የሰረቅሽው ፓሊስ ነው ምጠራልሽ እያለች ስትጮህ በአጋጣሚ በክፍሉ በር ሲያልፉ የሰሙት የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ከተፍ ይላሉ፡፡ ይህን ጊዜ ልጅቷ የባሰ ድንጋጤና ፍርሃት እያንቀጠቀጣት “እባክሽ ይቅር በይኝ እኔ ሌባ አደለሁም ከፈለግሽ እንኪ ፈትሽኝ ግን እዚህ ተማሪዎች ፊት አደለም” እያለች መምህሯ እግር ስር ወድቃ ልመናዋን ቀጠለች፡፡ መምህሯ ግን የተማሪዋን ስሜት ለአፍታ ቆም ብላ ለመረዳት ከመሞከር የከፋ ስሜት ውስጥ ሆና እየደነፋች ነው፡፡

በዚህ ጊዜ በእድሜ ጠና ያሉት ሴት ዳይሬክተር “ቆይስኪ መምህር ምን እንደተፈጠረ ንገሪኝ” ብለው ዳይሬክተሯ፣ መምህሯንና ተማሪዋን ወደ ቢሮ ወሰዷቸው፡፡ ከዛም ልጅቷን በተረጋጋ ሁኔታ እንድትቀመጥ ቢያደርጉም መምህሯ ግን እስካሁን መረጋጋት አልቻለችም፡፡ ይሄኔ በመምህሯ ድርጊት ጥቂት ብስጭት ያላቸው ዳይሬክተሯ መምህሯን ገላመጠው ዝም እንድትል ካደረጉ በኋላ ልጅቷን እረጋ ብለው "ቦርሳው ውስጥ ምንድነው ያለው" ብለው ጠየቋት፡፡ ልጅቷም "ቦርሳው ውስጥ ያለው ተማሪዎች በልተው የጣሉት ትርፍራፊ ነው" አለች በህፍረት እየተሸማቀቀች፡፡ ዳይሬክተሯም

በመገርምና ባለማመን ስሜት "እንዴት እንዲህ ይሆናል" ሲሉ ጠየቋት። እሷም ለወንድሞቼ ልወስድላቸው ብየ ነው አለች፤ አንገቷን ደፍታ በሚያሳዝን ሁኔታ ቅስሟ ተሰብሮ። ይህን ጊዜ ዳይሬክተሯ ከመቀመጫቸው ተነስተው ተጠጋትና ፀጉሯን እየደባበሱ "ኣይዞሽ የኔ ልጅ ተረጋግተሽ ስለ አባትሽና ስለ እናትሽ ንገሪኝ" አሏት።

ይህች ኣንዲት ፍሬ ልጅ እንባዋ እየወረደ እንዲህ ኣለች "ኣባቴ በሹፍርና ነበር እሚያስተዳድረን በኋላ ግን በሃሽሽ ተጠርጥሮ ወህኒ ቤት ገባ። እናቴም ብትሆን ምንም ገቢ ያልነበራት ስትሆን ያባቴን መታሰር ስትሰማ እራሷን ስታ ሆስፒታል ገባች። በዚያው የተነሳ ሽባ ሁና ቀረች። ታዲያ ሁለት ጨቅላ ወንድሞች ኣሉኝ፡፡ ቤት ነው ጥያቸው የመጣሁት ዘመድ ስለሌለን ዘወር ብሎ እሚያየን ባለመኖሩ ነው፤ እሚላስ እሚቀመስ የለንም። ታዲያ ይችን ፍርፋሪ ወስጄ ህይወታቸውን ብታደጋት ብዬ አሰብኩና ተማሪዎች አስተርፈው የጣሉትን ሳያዩኝ ለቃቅሜ ቦርሳየ ውስጥ ኣስገባሁ። ይሄን ነው ያደረኩት። እናም እባካችሁ ለተማሪዎች እንዳትነግሩብኝ። ትምህርቴንም ቢሆን አቋርጣለሁ። ብቻ አትናገሩብኝ" እያለች አንጀት በሚያላውስ ሁኔታ እንባዋን በአራት መንታ እያዘነበች ችግሯን ምንም ሳትደብቅ በልጅ አንደበቷ እየተኮላተፈች ለማስረዳት ሞከረች!

አይደለም በዚህች ጨቅላ ህጻን ይቅርና ለአዋቂ ሰዎች እንኳን ለመቋቋም ፈታኝ የሆነውን ችግሯን እንደ ወንዝ ጅረት ከሚፈስ እንባ ጋር ታጅቦ የሰሙት እኚህ አስተዋይ ዳይሬክተሯ እጅጉን ልባቸው ተሰበረ፤ እንባቸውን መቆጣጠር አቃታቸው፤ በቅጽበት ተንደርድረው ልጅቷን አቅፈው እህህህ ብለው አለቀሱ። በዚህ መሀል ታዲያ ሁሉንም ከዳር ቆማ ስትሰማ የነበረችው የክፍሏ መምህር በድርጊቷ እጅግ መራር ጸጸት ተሰማት። እዛው በቆመችበት ታለቅስ ጀመር። እንደ ዳይሬክተሯ እቺን ሚስኪን ተማሪ አቅፏ ውስጥ አድርጋት ልታጽናናት ብትሻም በክፍል ውስጥ በተማሪዎች ፊት ልጅቷን ያደረገችውን ስታሰበ አፈረች፤ አንገቷን አቀረቀረች። ዳይሬክተሯም የመምህራን ሁኔታ በድንገት ተመለከተው ስለነበር ወደ መምህሯ ተጠግተው ልጅቷን ይቅርታ እንድትጠይቅ ካደረጉ በኋላ እንዲህ አሏት። "ምንጊዜም በህይወታችን እውነቱን ቀርበን ሳናጣራ በሰዎች ላይ በጭፍን መፍረድ አልያም ተገቢ ያልሆነ ስም መስጠት ውሎ ሲያድር እውነቱን የተረዳን እለት ጸጸት ስለሚሆንብን ሁሌም እርግጠኛ ባልሆንበትና በማናውቀው ጉዳይ አስተያየት፣ ውሳኔና ፍርድ ለመስጠት አንቸኩል" አለቻቸው።

ልጆች ነገን ብሩህ ተስፋ ሰንቀው እንዲያድጉ እኛም ብንሆን ልናስብ የሚገባን በዝምድናም ይሁን በሌላ ሁኔታ ለምናውቃቸው ልጆች ብቻ ሳይሆን ያለምን መድሎ ሁሉንም እንከባከባቸው፡፡ ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ የተቸገሩ ህጻናትንም ሆነ ማንኛውም እርዳታን የሚሻ ሰው ሲገጥመን ከፈጣሪ በታች በምድር ላይ ከኛ ከሰዎች በላይ የሚቀርባቸው ማንም የለምና በሰብአዊነት እናስብላቸው፡፡

ተማሪዎች የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች በትኩረት ተመልክታችሁ በክፍት ቦታዎች ሊገቡ የሚችሉ ምን አይነት ቃላት እንደሆኑ አስረዱ፡፡

1. የዋሁ ______ በሆዱ ቂም አይቋጥርም፡፡
2. በጣም ______ ልጅ ወደትምህርት ቤት ሲሄድ አየሁት፡፡
3. መኮንን ዘወትር መጽሐፍ ማንበብ _______ ፡፡
4. ክድጃ ወደቤቷ ስትሄድ እንደአብነት_______ ወደቀች፡፡
5. ያ ተማሪ ____ቤተመጻሕፍት ሲሄድ ወንድሙን አገኘው፡፡

ተማሪዎች በክፍት ቦታዎች ሊገቡ ስለሚችሉ ቃላት አብረዋችሁ ከተቀመጡ ተማሪዎች ጋር ተወያዩ፡፡ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ከየወንበሩ አንድ ተማሪ እየተነሳ ያስረዳ፡፡ መልካም!!! በገለጻችሁት መሰረት በጥያቄ ቁጥር አንድ መግባት የሚችለው የቃል ክፍሉ ስም የሆነ ቃል ነው፡፡ ቀድሞ የመጣው ቃል “የዋሁ” የሚለው ቃል በመሆኑ ቀጥሎ የሚመጣው ቃል ስም እንዲሆን ያስገድደዋል፡፡ ሁለተኛው ጥያቄ ላይ ደግሞ መጠንን የሚገልጸው የቅጽል ገላጭ (በጣም) በመኖሩና ከክፍት ቦታው ቀጥሎ የቃል ክፍሉ ስም የሆነ ቃል በመኖሩ ምክንያት በክፍል ቦታው ቅጽል እንደሚገባ መረዳት ይቻላል፡፡ በጥያቄ ቁጥር ሶስት ላይ ደግሞ ጅምር ዓረፍተነገሩ ላይ ሁነትን የሚገልጽ ግስ ይገባል፡፡ በጅምሩ ዓረፍተነገር ድርጊቱ፣ ሁነቱ ወይም ኑረቱ ባለመገለጹና ማሰሪያ አንቀጽ ስላልተሰጠው በማሰሪያ አንቀጽት የሚገባ ግስ እንደሚጎድለው መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመጨረሻም በአምስተኛው ዓረፍተነገር ሲሄድ የሚለው ጥገኛ ሀረግ በመሙያነት አቅጣጫን የሚያመለክት መስተዋድዳዊ ሀረግ ስለሚያስፈልገው መስተዋድድ (ወደ) እንደሚገባ መረዳት ይቻላል፡፡

ከአምስቱም ዓረፍተነገሮች ቃላት ከሚገኙበት ዐውድ አንጻር የቃልክፍሎችን መለየት እንደሚያስችል ሁላችሁም እንደተረዳችሁ እምነቴ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ከይዘትና ከሰዋስዋዊ አገልግሎት አንጻር የንግግር ክፍሎችን መከፋፈል እንደሚቻል ልትገነዘቡ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ከይዘት አንጻር ለአንድ ነገር፣ ቁስ፣ ሰው ወይም እሳቤ መጠሪያ በመሆን የሚያገለግል ስም በመባል ይጠራል (ዝርዝር ማብራሪያውን ከመማሪያ መጽሐፋችሁ ላይ አንብቡ)፡፡

የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች በትኩረት በማንበብ ከስራቸው የተሰመረባቸውን ቃላት የሚገኙበትን ቦታ መሰረት በማድረግ የቃል ክፍላቸውን ለዩ፡፡

1. አያሌው ዛሬ ጧት መረብ ኳስ ተጫወተ፡፡
2. ጠይሙ ሙስጠፋ ከነገወዲያ የትምህርት መሣሪያዎችን ይገዛል፡፡
3. በጣም ጠይሙ ልጅ ትምህርቱን ተምሮ ጨረሸ፡፡
4. ልጁ እንደእህቱ ከፉኛ ታመመ፡፡
5. ትርሲት ወደቤቷ ሮጠች፡፡

ቃላት በሥርዓት ተዋቅረው ከቃላት በላይ የሆነ ሌላ መዋቅር ይመሰርታሉ፡፡ ይህ ቃላት በሥርዓት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ሐረግ ይባላል፡፡ የሐረግ መዋቅር መሠረት ቃላት ናቸው፡፡ የሐረጉ ዓይነት የሚወሰነውም ሐረጉን እንደሚመሰርቱት የቃል ክፍል ነው፡፡ የአማርኛ የሐረግ ዓይነቶች በአማርኛ አምስቱ የቃል ክፍሎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡

| የቃል ክፍሎች | የሐረግ ዓይነት |
|---|---|
| ስም | ስማዊ ሐረግ |
| ቅፅል | ቅፅላዊ ሐረግ |
| ግስ | ግሳዊ ሐረግ |
| መስተዋድድ | መስተዋድዳዊ ሐረግ |
| ተውሳከ ግስ | ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ |

ከላይ እንደቀረበው እንደቃል ክፍሎቹ ዓይነት ልዩነት የሐረጎቹም ዓይነት

ይለያያል። ለሐረጎቹ መሠረት የሆኑት ቃላት የሐረጉ መሪዎች ናቸው። በዚህም ምክንያት ማንኛውም ሐረግ መሪ ቃል አለው። ስለሆነም የስማዊ ሐረግ መሪ ስም፣ የቅፅላዊ ሐረግ ቅፅል፣ የግሳዊ ሐረግ ግስ፣ የመስተዋድዳዊ ሐረግ መስተዋድድ፣ የተውሳከ ግሳዊ ሐረግ ተውሳከ ግስ ናቸው።

መሪ የአንድ ሐረግ አይቀሬ አካል በመሆኑ ሁሉም የሐረግ ዓይነቶች መሪ አላቸው። የአንድ ሐረግ መሪ ከተመሪ አበር ተዋቃሪዎች በስተቀኝ ወይም በስተግራ ሊገኝ ይችላል። መሪው በስተቀኝ የሚገኝ ከሆነ ቀኝ መሪ፣ በስተግራ የሚገኝ ከሆነ ደግሞ ግራ መሪ ይባላል። የአማርኛ የሐረግ ዓይነቶች ቀኝ መሪ ሲሆኑ፣ መስተዋድዳዊ ሐረግ በተጨማሪ ግራ መሪም ሆኖ ይገኛል።

ሀ. ስማዊ ሐረግ፣ መሪው ስም የሆነ የሐረግ ዓይነት ሲሆን፣ በመሪ ብቻ ወይም በመሪና በተመሪዎች ቅንጅት ሊፈጠር ይችላል።

ምሳሌ፣ የሃምሌ ፀሐይ ነብር [ሁለት ፍየሎች ገደለ] የመርሳ ብርቱካን ነብር - ስማዊ ሐረግ (በመሪ ብቻ) የስንዴ ቆሎ

ለ. ቅፅላዊ ሐረግ፣ መሪው ቅፅል የሆነ የሐረግ ዓይነት ሲሆን፣ ከተለያዩ ተዋቃሪዎች ጋር በመቀናጀት የሚመሠረት ነው።

ምሳሌ፣ በጣም ትልቅ [ድንች] እጅግ ትሁት [ሰው] የልጅ አስተዋይ

ሐ. ግሳዊ ሐረግ፣ መሪው የድርጊት፣ የሁነት ወይም የኑረት ግስ የሆነ የሐረግ ዓይነት ሲሆን፣ ከተለያዩ አጃቢዎች ጋር እየተቀናጀ የሚመሠረት ነው።

ምሳሌ፣ ቤት ገዛ።

መምህር ሆነ። ቢሮ ውስጥ አለ።

መ. ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ፣ ተውሳከ ግስን መሪ ያደረገ የሐረግ ዓይነት ሲሆን፣ በመሪው ብቻ ወይም የማነፃፀር ባሕርይ ካለው መስተዋድዳዊ ሐረግ ጋር በመዋቀር የሚመሠረት ነው።

ምሳሌ፣ እንደእሾህ ክፉኛ [ወጋኝ]

ሰውየው ምንኛ [ጠግቧል]

ዳገቱን ጅልኛ [ወጣው]

መ. መስተዋድዳዊ ሐረግ፣ መስተዋድድን መሪ ያደረገ የሐረግ ዓይነት ሲሆን፣ ከስማዊ ሐረግ ወይም መስተዋድዳዊ ሐረግ ጋር በመዋቀር የሚመሠረት ነው፡፡ ሐረጉ፣ መስተዋድድን ግራ፣ ቀኝ፣ ግራም ቀኝም መሪ የሚያደርግ የሐረግ ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌ፣ ግራ መሪ ሲሆን፣ ወደ ወልድያ [እሄዳለሁ]

ከ ትልቁ ቤት [ወጣች]

ቀኝ መሪ ሲሆን፣ አልጋው ስር [ፈልገው]

ወንበሩ ላይ [እንዳትወጪ]

ግራም ቀኝም መሪ ሲሆን፣ ከ ዛፉ ላይ [ውረድ]

እስከ ቤቱ ድረስ [ሸኘሁት]

ከቀረበው ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ሐረጎች ከብረዋቸው ከሚዋቀሩ ሀረጎች በመነሳት የሀረጎችን አይነት መለየት እንደሚቻል ነው፡፡ የአንድ ዓረፍተነገር አይቀሬ ተዋቃሪ የሚባሉት ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ናቸው፡፡ ሌሎች ሀረጎች በሁለቱ ሀረጎች ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ ናቸው፡፡ በዓረፍተነገሩ ስማዊ ሀረግ (ባለቤት) ውስጥ ተውሳከግሳዊ ሀረግ እንዲሁም በግሳዊ ሀረግ ውስጥ ቅጽላዊ ሀረግ የመካተት እድል እንደሌለው መረዳት መቻላችሁ የሀረግ አይነቶችን ለመለየት የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ይህም የሚሆነው የስም ገላጭ ቅጽል፣ የግስ ገላጭ ተውሳከግስ ከመሆኑ አንጻር የመጣ ነው፡፡ ይህም በዓረፍተነገር ውስጥ የሚገኙበት ቦታ ሀረጎችን እንድለይ የማድረግ እድሉ ከፍ ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

፩. የሚከተሉትን ሐረጋት፣ በሐረግ ዓይነታቸው ለዩ፡፡

ሀ. ከብቶች <u>ከትልቁ ዛፍ አጠገብ</u> ተኝተዋል፡፡

ለ. እስክንድር <u>የልጅ ዐዋቂ</u> ነው፡፡

ሐ. <u>ቀንዳም ጥጃ</u> እድሜ አይኖረውም፡፡

መ. <u>በጣም የዋሁ</u> ልጅ ቤተሰቦቹን ይጎበኛል፡፡

ሠ. ተሰማ <u>ክፉኛ ወደቀ</u>፡፡

ረ. <u>እንደሯጭ ቶሎ</u> ደረሰ፡፡

፪. የሚከተሉትን ቃላት በማዋቀር ዐራት ስማዊ ሐረጎችን መሥርቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| እንደ መብረቅ ፈጥኖ | ትልቅ ዛፍ | ለብሳ መጣች |
| በሀገር የለም | የጥጥ ቀሚስ | እንደሱ የወንድ ፈሪ |
| ከቤቱ በላይ | ወተት ይወዳል | እንደድመት |
| በነፋስ ተገንድሷል | ኳሷን ጠለዛት | ንቦች ሰፍረዋል |

ተማሪዎች ተግባራትን በታዘዛችሁት መሰረት በመስራታችሁ በጣም አስደስታችሁኛል፡፡ ከተግባራቱ አንድን ሀረግ ለመለየት ሌላኛው ሀረግ ምን አስተዋጽ አበረከተላችሁ? ሀረጎችን ለማዋቀርስ የተማራችሁት ትምህርት በምን መልኩ አገዛችሁ? መልካም!! ከዚህ ክፍለጊዜ ውጭም ተመሳሳይ የሆኑ ተግባራትን በመስራት ልምምድ አድርጉ፡፡